18ኛ አመት ቁጥር 17

18th Year No 17

ባህር ዳር ሐምሌ 19 ቀን 2005 ዓ.ም

Bahir Dar 26th, July 2013

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

# ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG

## OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA



| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 39.134 Price | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box |



| ማውጫ | Contents |
|---|---|
| **ደንብ ቁጥር 117/2005 ዓ.ም** | **Regulation No.117/2013** |
| በአማራ ብሂራዊ ክልላዊ መንግስት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ምዝገባና አስተዳደር መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | The Amhara National Regional State Charities and Societies Registration and Administration Determination, Council of Regional Government Regulation |

| ደንብ ቁጥር 117/2005ዓ.ም | REGULATION No.117/2013 |
|---|---|
| በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ምዝገብና አስተዳደርን ለመወሰን የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | A REGULATION ISSUED BY THE COUNCIL OF THE REGIONAL GOVERNMENT TO PROVIDE FOR THE DETERMINATION OF THE REGISTRATION AND ADMINISTRATION OF THE CHARITIES AND SOCIETIES IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE. |

በክልሉ ውስጥ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ኮሚቴዎችን እንዲሁም ማህበራትን ለማቋቋምም ሆነ ለማፍረስ የሚያስችሉ መስፈርቶችን በዝርዝር ህግ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በግልና በማህበር መልክ በመደራጀት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ማቋቋም ወይም መብቶቻቸውንና ጥቅሞቻቸውን ማስከበር እንዲሁም ሲቪል ማህበራትን ማደራጀት ለሚፈልጉ የህብረተሰብ ክፍሎች ግልፅ አሰራር በማስፈን እነዚሁ ድርጅቶችና ማህበራት በክልሉ ውስጥ የሚስፋፉበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ፣

የአማራ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና የክልሉን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራት ለመመዝገብና ለማስተዳደር በወጣው አዋጅ ቁጥር 194/2004 ዓ.ም. አንቀፅ /107/ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

Whereas, it has been found necessary to provide in specific law for a set of requirements enabling to either to establish or dissolve the charities and committees as well as societies in the Regional State;

Whereas, it has been necessary to create a favorable condition for those sections of the society to form charities or enforce their rights and benefits as well as to organize civil societies either privately or by association and see to it that such institutions are promoted through the Region having put in place a transparent working procedure thereof;

Now, THEREFORE, the Council of the Amhara Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of Art. 58 Sub-Art. 7 of the Revised National Regional Constitution and Art. 107 Sub. Art. 1 of the Regional Proclamation No.194/2012 enacted to provide for the Determination of the Registration and Administration of Charities and Societies, hereby issues this regulation as follows:

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ምዝገባና አስተዳደር መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 117/2005 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

1. የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፣

   ሀ. “ንብረት ማጣራት” ማለት ንብረቱ በሕግ አግባብ እንዲጣራ ውሳኔ የተላለፈበትን የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር ሃብትና ዕዳ የመለየት ሂደት ነው፡፡

   ለ. “ንብረት ማስተላለፍ” ማለት የሂሳብ መግለጫ ከቀረበ በኋላ የተጣራውን ኃብትና ንብረት ለሌላ ወገን የማስተላለፍ ሂደት ነው፡፡

   ሐ. “የገቢ ማስገኛ ስራ” ማለት አንድ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር በቢሮው በሚሰጠው የገቢ ማስገኛ ሥራ ፈቃድ መሠረት በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ባለቤትነት ሥር የሆነ ለትርፍ የሚቋቋምና የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ከተመዘገበበት ዓላማ እና ከተሠማራበት የሥራ መስክ ጋር

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This regulating may be cited as “The Charities and Societies Registration and Administration Determination, Council of Regional Government Regulation No. 117/2013.”

### 2. Definitions

1. Unless the context requires otherwise, in this regulation:

   A. “Property Inspection” shall mean a process of sorting out of the assets and liabilities of a charity or society against which a decision has been rendered so that its property should lawfully be inspected thereof.

   B. “Transfer of Property” shall mean a process of passing the assets and properties inspected thereof on to another party following the submission of an accounting statement to that effect.

   C. “Income Generating Activity” shall mean a business activity to be carried out for gain pursuant to an income generating activity permit issued by the Bureau under the ownership of a charity or society, having to do with an objective for which the charity or society is registered and directly related to the

ቀጥታ ግንኙነት ያለውና ትርፍ ለማግኘት የሚሰራ የንግድ እንቅስቃሴ ነው፡፡

መ. “ፈቃድ” ማለት በሌሎች ህጎች ለንግድ፣ ለኢንቨስትመንት እና ሌሎች ትርፍ ለማግኘት ለሚሰሩ ስራዎች የተቀመጡ የምዝገባና የፈቃድ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ ለመሰማራት እንዲችሉ በቢሮው የሚሰጥ የፅሁፍ ማረጋገጫ ነው፡፡

ሠ. “የሂሳብ መግለጫ” ማለት ማናኛውም የበጐ አድራጐት ድርጅት፣ ማህበር ወይም የበጎ አድራጎት ኮሚቴ የሀብትና እዳ ሚዛን ትንተናውን፣ በዓመቱ የሰበሰበው የገቢ መጠንና ምንጩን እንዲሁም የዓላማ ማስፈፀሚያና የአስተዳደራዊ ወጪዎቹን ዝርዝር በበጀት አመቱ መጨረሻ ተቀባይነት ባለው አሰራር ለቢሮው ሠርቶ የሚያቀርበው የሂሳብ ሰነድ ነው፡፡

ረ. “አዋጅ” ማለት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የወጣው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት መመዝገቢያና ማስተዳደሪያ አዋጅ ቁጥር 194/2004 ዓ/ም ነው፡፡

tasks in which it engages so as to function for the generation of profit there from.

D. “L**icense**” shall mean, without prejudice to the requirements of license and registration specified under other laws for business, investment and other activities to be undertaken in order to obtain profit, a written certificate to be issued by the Bureau so that charities and societies may be able to engage in income generating activities.

E. “Statement of Account” shall mean an accounting document which any charity, society or a charity committee would provide an analyzed balance sheet of its assists and liabilities, the amount of annual income it may have collected along with its sources as well as the details of its operational and administrative expenses to the Bureau, having same prepared an acceptable working procedure.

F. “**Proclamation**” shall mean the Charities and Societies Registration and Administration Proclamation No.194/2012 issued by The Amhara National Regional State.

2. በዚህ ደንብ ውስጥ "የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት" ወይም "የኢትዮጵያ ማህበር"፣ "የኢትዮጵያ ነዋሪዎች በጎ አድራጎት ድርጅት" ወይም "የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ማህበር" እና "የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅት"፣ "ከውጭ ምንጭ የሚገኝ ገቢ"፣ "ብዙሀን ማህበራት"፣ "ቢሮ" እና "የቢሮ ኃላፊ"፣ "የስራ መሪ"፣ "የሥራ ቦታ"፣ "ሕዝባዊ መዋጮ"፣ "መተዳደሪያ ደንብ"፣ "የበጀት ዓመት"፣ "የዘርፍ አስተዳዳሪ"፣ "አስተዳደራዊ ወጪ"፣ "የሃይማኖት ድርጅት" እና "ሰው" የሚሉት ቃላትና ሃረጎች በአዋጁ አንቀጽ 2 ስር የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

2. Such terms and phrases in this Regulation as the "Ethiopian Charities" or "Ethiopian Societies", Ethiopian Residents Charities" or "Ethiopian Residents Societies" and "Foreign Charities", "Income from Foreign source", "Mass-Based Societies", "Bureau" and "Bureau Head", "Officer", "Place of Work", "Public Collection", "Rule", "Budget Year", "Sector Administrator", "Administrative costs", "Religious Organization" and "Person" shall have the same meanings as are accorded to them under Art. 2 of the Proclamation.

### 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በክልሉ ተመዝግበው በክልሉ ውስጥ ብቻ በሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ማህበራት እና በጎ አድራት ኮሚቴዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

### 3. Scope of Application

This regulation shall be applicable to only those charities, societies and charity committees having been registered by the region and operating therein.

## ክፍል ሁለት
## ስለምዝገባ

## PART TWO
## REGISTRATION

### 4. ለመደበኛ ምዝገባ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

1. በአዋጁ አንቀጽ 63 ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ደንብ መሰረት የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡-

### 4. Application for Normal Registration

1. Without prejudice to what has been specified under Art. 63 Sub-Art. 3 of the Proclamation, an application registration to be submitted in pursuance of this regulation shall contain the following particulars of information:

ሀ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሊሠራ ያሰበባቸውን የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማና የቀበሌ አስተዳደሮች ዝርዝር፣

ለ. ቢሮው ባዘጋጀው ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ ለመመራት የተሰጠ ስምምነት ወይም በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ መስራቾች የተፈረመ መተዳደሪያ ደንብ፤

ሐ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የገንዘብ ምንጭ እና ከመቶው ምን ያህሉ ከኢትዮጵያ ውስጥ እንደሆነ ወይም እንደሚሆን የሚያሳይ መግለጫ፤

መ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ መስራች አባላትና የሥራ መሪዎች፣ ሙሉ ስም፣ ዕድሜ፣ ጾታ፤ የመኖሪያ አድራሻና የትምህርት ደረጃ

ሠ. ሊቋቋም የታሰበውን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ዓይነት፤

ረ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሊጠቀምበት የሚፈልገው ምልክት ካለ ይህንኑ፤ እና

ሰ. በቢሮው የሚጠየቁ ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎች፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ መሥራቾች፣ ባለአደራዎች ወይም ተወካዮች የፈረሙበትና

A. the list of the zonal, Woreda, urban and Kebele Administrations in which the charity or society intends to operate;

B. a consent rendered to the Bureau in view of being guided by the model rules which the Bureau may have prepared thereof or a rule duly signed by the founders of the charity or society;

C. a statement showing the source of funds for the charity or society and what portion in percentage of such funds has be or might be generated from within Ethiopia;

D. full name, age, sex, residential address and educational status of the founding members and officers of the charity or society;

E. the type of a charity or society intended to be formed;

F. a symbol, if any, which the charity or society desires to use; and

G. Such other information as might be required by the Bureau in view of their relevance.

2. The application submitted pursuant to Su-Art. 1 of this Article hereof shall be one signed by the founders of charity or society, trustees or representatives and

በውስጡ የተካተቱት መረጃዎች እውነትና ትክክል ስለመሆናቸው ማረጋገጫ የተሰጠበት መሆን ይኖርበታል፡፡

thereby confirmed that the information contained therein is true and accurate.

3. ቢሮው የፈቃድና ምዝገባ ጥያቄውን ውድቅ ያደረገው እንደሆነ ይህንኑ ከነምክንያቱ በጽሁፍ ገልጾ ለአመልካቹ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

3. Where the Bureau has rejected the application for license and registration, it shall notify such an action with justification in writing and communicate same to the applicant;

4. ቢሮው ምዝገባ የሚያካሂደው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን እና አግባብነት ያለውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ይሆናል፡፡

4. The Bureau shall carry out the registration by having exacted the service charge as is duly prescribed in the schedule annexed to this regulation.

## 5. በበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ማህበራትና ኮሚቴዎች ስያሜ ላይ ስለሚደረግ ለውጥ

ቢሮው የአመልካችን ወይም አስቀድሞ የተመዘገበን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ስያሜ እንዲቀየር የሚያደርገዉ፡-

1. ከሌላ አስቀድሞ ከተመዘገበ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ስም ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተቀራራቢ ሲሆን፣

2. በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ከሰፈሩት እውነተኛ ዓላማዎችና ሥራዎቹ አንጻር ህብረተሰቡን ሊያሳስት የሚችል ሲሆን ነው፡፡

## 5. Alteration Made to the Designation of Charities, Societies and Committees

The Bureau shall cause the alteration of designation of an applicant or a previously registered charity or society where:

1. it is as the same as or similar to the name of any other charity or society registered previously;

2. It is likely to mislead the community in respect of the true nature of the purposes and activities specified in its rules.

## 6. መተዳደሪያ ደንቡ ስለሚይዛቸው ዝርዝሮች

1. የማንኛውም በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መተዳደሪያ ደንብ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

ሀ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን ስያሜ፣ አድራሻና ዓላማ፤

ለ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን አደረጃጀት፤

ሐ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የበጀት ዓመት፤

መ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን ገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት፤

ሠ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ የሥራ መሪዎች የሚመረጡበት ወይም የሚቀጠሩበት ሥርዓት፣ ሥልጣንና ተግባራቸው እንዲሁም የአገልግሎት ዘመናቸው፤

ረ) አባላት ወይም የሥራ መሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ አባልነታቸው ወይም የሥራ መሪነታቸው ቀሪ ስለሚሆንበት ሁኔታ፤

ሰ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ አመራር አካላት የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት፤

## 6. Particulars of the Rule

1. The rules of any charity or society shall contain the following:

A. designation, address and objectives of the charity or society;

B. organizational structure of the charity or society;

C. the budget year of the charity or society;

D. the financial administration and utilization system in place for the charity or society;

E. the procedure through which the officers of the charity or society are selected or employed, their powers and duties as well as their tenure;

F. the conditions in which members or officers of the charity or society might resign or terminate their membership thereof;

G. meeting and decision making procedure put to use by the management organs of the charity or society;

ሸ) አመልካቹ ማህበር የሆነ እንደሆነ አባላትን የሚቀበልበትና የሚያሰናብትበት ሥርዓት፣ የአባላቱ መብቶችና ግዴታዎች እንዲሁም የሚያደርጉት መዋጮ መጠን፤

ቀ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ስለሚሻሻልበት ሥነ ሥርዓት፤

በ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የገቢ ምንጮች፤

ተ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሲፈርስ ተፈጻሚ ስለሚደረገው ሥነ-ሥርዓት ፤እና

ኀ) ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ከማህበሩ ዓይነትና ጸባይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው እና በቢሮው በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች ጉዳዮች፡፡

2. ቢሮው ባዘጋጀው ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ ከመጠቀም ይልቅ የራሱን መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅቶ ለምዝገባ የቀረበ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ለምዝገባ አገልግሎት ከሚጠየቀው ክፍያ በተጨማሪ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን የመተዳደሪያ ደንብ ማስገምገሚያ ክፍያ ይከፍላል፡፡

## 7. ወዲያው ስለሚፈፀም ምዝገባ

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የቢሮውን ሞዴል

H. where the applicant is a society, the procedure in which it admits or dismisses its members, the rights and obligations of the members as well as the amount of contributions payable thereof;

I. the procedure through which the rules of the charity or society are amended;

J. sources of income of the charity or society;

K. the procedures to be applied where the charity or society is dissolved; and

L. other matters having to do with the type and character of the charity or society and to be determined by a directive of the Bureau.

2. A charity or society intending to utilize the rules prepared by itself in preference to the model rules prepared by the Bureau shall, upon showing up for registration, pay the charge prescribed for vetting such rules as specified in the schedule annexed to this regulation in addition to the amount required for the registration service.

## 7. Immediate Registration

1. Without prejudice to Art. 4 of this Regulation hereof, any Ethiopian

መተዳደሪያ ደንብ ለመጠቀም ፈቃደኛ የሆነ፣ የፕሮጀክት መግለጫ ማቅረብ የማይጠበቅበትና ሕብረት ያልሆነ ማንኛውም የኢትዮጵያ ማህበር ወዲያውኑ ይመዘገባል፡፡

2. ወዲያውኑ መመዝገብ የሚፈልጉ የኢትዮጵያ ማህበራት የሚገለገሉባቸውን ሞዴል መተዳደሪያ ደንቦች ቢሮው ያዘጋጃል፡፡

3. ወዲያውኑ የተመዘገበ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ መልክ ቀድሞውኑ መመዝገብ ያልነበረበት ሆኖ ሲገኝ፡-

ሀ) መደበኛ ምዝገባ ለማድረግ የሚጠየቁ መስፈርቶችን እንዲያሟላ ከተደረገ የተመዘገበበት ቀን ሳይቀየር በአዋጁ አንቀጽ 63 መሠረት እንደተመዘገበ ይቆጠራል፤

ለ) ለመደበኛ ምዝገባ የሚያስፈልገውን ቀሪ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ቢኖርም ቢሮው በአዋጁ አንቀጽ 87 የተሰጠውን ስልጣን በተጠቀሰው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ላይ ከመፈፀም አያግደውም፡፡

society that is willing to use the model rules prepared by the Bureau, not anticipated to submit a project document as well as which does not happen to be a consortium shall be registered immediately.

2. The Bureau shall prepare the model rules which the Ethiopian societies desiring to register immediately might utilize thereof.

3. Where it is found out that a charity or society which has immediately been so registered should not have, from the very outset accordingly, it shall:

A. be considered to have been duly registered in accordance with Art. 63 of the proclamation without altering the date of its registration if it is made to fulfill the requirements set out in order to carry out normal registration;

B. be caused to effect the remaining balance of the service charge required for the normal registration.

4. Notwithstanding the provision of Sub-Art.3 of this Article, it may not bar the Bureau from exercising its power vested in it under Art. 87 of the proclamation on the said charity or society.

5. ቢሮው ወዲያውኑ ስለሚመዘገቡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 8. ህብረት ስለመመስረት

1. ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት የጋራ ዓላማዎችን ለማሳካት የሚፈጠር ማናቸውም ህብረት እንደ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መመዝገብ አለበት፡

2. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ለማቋቋም በአዋጁና በደንቡ ላይ የተመለከቱትና አግባብነት ያላቸው መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ህብረት ለመመስረት የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል፡-

   ሀ) በህብረቱ መስራች አባላት የተፈረመ መተዳደሪያ ደንብ፣

   ለ) ህብረቱን ለመመስረት መስራች አባላት የተስማሙበት ቃለ ጉባዔ፣

   ሐ) በቢሮው የተሰጠና የታደሰ የምዝገባ ሰርተፊኬት፣

   መ) እያንዳንዱ የህብረቱ አባል በየራሱ የበላይ አካል ህብረቱን ለመመስረት ወይም የህብረቱ አባል ለመሆን ውሳኔ ያሳለፈበት ቃለ ጉባዔ፣

5. The Bureau may issue a specific directive regarding those charities and societies to be registered immediately.

## 8. Formation of Consortium

1. Any consortium to be formed by two or more charities or societies in order to achieve common purposes shall be registered in the same manner as any charity or society.

2. Without prejudice to the appropriate requirements indicated by the proclamation and the regulation with a view to establish a charity or society, the following pre-requisites shall be fulfilled so as to form a consortium,:

   A. a rule duly signed by the founding members of the consortium;

   B. a minute agreed upon by the founding members of the consortium;

   C. a certificate of registration issued and renewed by the Bureau;

   D. a minute showing that each member of the charity has passed the decision of its superior body to form the consortium or to be a member of thereof;

3. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከማህበራት ጋር ህብረት መመስረት አይችሉም፡፡

4. ሕብረት ለመመስረት የሚፈልጉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ለመደበኛ ምዝገባ የተመለከተውን ክፍያ መፈፀም ይኖርባቸዋል፡፡

## 9. ምዝገባን አስመልክቶ ስለሚቀርቡ ተቃውሞዎች

ማንኛውም ሰው አንድ አመልካች በበጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት መመዝገቡ ወይም የስም፣ የአርማ ወይም የምልክቶች ለውጥ ማድረጉ የሚጎዳው ሲሆን ምዝገባውን ወይም በመዝገብ ውስጥ የሚሰፍረውን ማናቸውንም ዝርዝር ሊቃወም ይችላል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ተቃውሞ የሚቀርበውና የሚወሰነው ቢሮው በሚዘረጋው ዝርዝር የአሰራር ሥርዓት መሠረት ይሆናል፡፡

## 10. በድጋሚ ስለሚደረግ ምዝገባ

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አዋጁ ከመጽናቱ በፊት የተመዘገቡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ያለምንም ክፍያ ቢሮው በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ በድጋሚ ይመዘገባሉ፡፡ ድጋሚ ምዝገባው የሚካሄድበት ዝርዝር በቢሮው ይወሰናል፡፡

3. No charities may form a consortium with societies.

4. Charities or societies desiring to form a consortium shall effect the payment prescribed for normal registration in the schedule annexed with this regulation.

## 9. Objections Submitted Against Registration

Where any person is to be affected by the forcible registration of a charity or society or by the act of its making alteration of name, emblem or symbols applying for same, he may object to the initiation of such registration or possible entry in the register. Such objection shall be made and decided thereon in accordance with the detailed working procedures to be put in place by the Bureau.

## 10. Re-registration

1. Without prejudice to what has been provided under Art. 4 of this Regulation hereof, charities and societies registered prior to the coming into force of the proclamation shall be re-registered free of charge in accordance with the schedule set by the Bureau. Particulars with which to carry out of the said re-registration shall be determined by the Bureau.

2. የድጋሚ ምዝገባው ውጤት ተግባራዊ የሚሆነው ድጋሚ ምዝገባው በተጠናቀቀበት ጊዜ ሳይሆን አዋጁ ከፀና ከአንድ ዓመት በኋላ ይሆናል፡፡

## 11. ምልክቶችን ስለማስመዝገብ

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሊጠቀምበት የወሰነውን አርማ ወይም ምልክት በጥቅም ላይ ከማዋሉ በፊት ለቢሮው ማቅረብና ማስመዝገብ አለበት፡፡
2. አርማ ወይም ምልክት ለማስመዝገብ የሚቀርበው ማመልከቻ የአርማውን ወይም የምልክቱን ቅጂ እንዲሁም አላማ፣ ቅርጽ፣ ይዘት፣ ቀለማትና ሌሎች አስፈላጊ ዝርዝሮችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡
3. ለምዝገባ የቀረበው አርማ ወይም ምልክት ተቀባይነት ያለው ሆኖ ከተገኘ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ በማስከፈል በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መዝገብ ዉስጥ እንዲገባ ይደረጋል፡፡
4. የአርማ ወይም የምልክት ምዝገባ ጥያቄውን ቢሮው ካልተቀበለው ምክንያቶችን ጨምሮ ማመልከቻው ተቀባይነት አለማግኘቱን ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

2. The effects of the re-registration shall be implemented one year after effective date of the proclamation, not at the time of the completion of the re-registration thereof.

## 11. Registration of Symbols

1. Any charity or society shall submit to the Bureau and thereby cause the registration of any emblem or symbol which it may have decided to its utilization thereof.
2. An application submitted for the registration of such emblem or symbol shall include a copy of the emblem or symbol as well as its objective, form, content, colors and such other particulars necessary therewith.
3. Where the emblem or symbol presented for the registration is founded to be acceptable, it shall be entered in the register of charities and societies upon payment of the fee prescribed in the schedule annexed to this Regulation hereof.
4. Where the Bureau has rejected the application for registration of an emblem or symbol, it shall notify such an action along with justification in writing and communicate same to the applicant.

5. በዚህ ደንብ አንቀጽ 15 ስር የተደነገገው ከአስፈለጊ ማስተካከያዎች ጋር ለአርማና ለምልክቶች ማሻሻልና መለወጥም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 12. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አደራ ጠባቂዎች

1. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት እንደተመሠረተ የሚቆጠረው የድርጅቱ መሥራች ወይም እርሱ የወከለው ሰው ወይም ቢሮው በአዋጁ መሠረት የአደራ ጠባቂ በሚሾምበት እና የተሾመው አደራ ጠባቂ በሹመቱ ተስማምቶ በተቀበለበት ቀን ነው፡፡
2. የአዋጁ አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ (3) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አደራ ጠባቂዎቹ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ድርጅቱን ለማስመዝገብ ጥያቄ ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ቢሮው ከአደራ ጠባቂነት እንዲነሱና በሌላ እንዲተኩ ያደርጋል፡፡
3. ቢሮው የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ከተቋቋመ በኋላ ባለው የሶስት ወር ጊዜ ውስጥ አደራ ጠባቂዎቹ የምዝገባ ማመልከቻ ያላቀረቡበት ምክንያት በቂ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን መስራች ወይም የሚመለከተውን የዘርፍ አስተዳዳሪ ሊያማክር ይችላል፡፡

5. The provisions laid down under Art.15 of this Regulation hereof shall, with the necessary adjustment, be applicable to the improvement and changes of the emblem and symbols.

## 12. Trustees of a Charitable Trust

1. A charitable trust shall be deemed to be formed on the day on which the founder of the charity or the person designated by him or the Bureau has appointed a trustee in accordance with the proclamation and the appointed trustee has consented to and accepted the appointment thereof.
2. Without prejudice to the provisions of Art. 59, Sub-Art.3 of the Proclamation, where the trustees fail to apply for the registration of the charitable trust within three months as of the constitution of same, the Bureau shall cause them to be removed from the status of their trusteeship and be replaced by other ones.
3. The Bureau may, in order to determine as to whether the reason for the failure of the trustees to apply for the registration within the period of three months from the formation of the charitable trust is sufficient or not, consult with the founder of the charitable trust or the sector administrator concerned.

## 13. ስለአደራ ጠባቂዎችና ሶስተኛ ወገኖች ግንኙነት

1. የአዋጁ አንቀጽ 60 ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አደራ ጠባቂዎች የምዝገባ የምስክር ወረቀት ከማግኘታቸው በፊት በስጦታ ወይም ኑዛዜ ላይ የተመለከተን ሀብት ባለይዞታነት ወይም ባለቤትነት ወደ አደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ለማስተላለፍ ከሚያስፈልጉ ድርጊቶች በስተቀር ሶስተኛ ወገኖችን የሚያካትቱ ማናቸውንም ሕጋዊ ድርጊቶች ማከናወን አይችሉም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የሰፈረውን ድንጋጌ አደራ ጠባቂዎች ከአደራ ጠባቂነት እንዲነሱና በሌላ እንዲተኩ ይደረጋል፡፡

3. አደራ ጠባቂዎቹ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተላልፈው የፈጸሙት ማናቸውም ድርጊት በአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ላይ ባደረሰው ጉዳት መጠን በአንድነት እና በነጠላ በፍታብሔር ተጠያቂዎች ይሆናሉ፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ አደራ ጠባቂዎች ለሚፈጽሙት ድርጊት የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ኃላፊነት አይኖርበትም፡፡

## 13. Relationship Between Trustees and Third Parties

1. Without prejudice to the provision of Art. 60, Sub-Art.3 of the Proclamation, no trustees of a charitable trust may be able to carry out any lawful activities involving third parties prior to acquisition of a certificate of registration with the exception of such acts as might be necessary for transfer of assets specified in a donation or will on to the possession or ownership of the charitable trust.

2. Trustees who have violated the provision stipulated under Sub-Art. 1 of this Article hereof shall be subject to be removed from the status of their trusteeship and replaced by others.

3. Trustees shall jointly and severally be liable in civil matters for any damage sustained to the charitable trust due to any acts committed in violation of Sub-Art. 1 of this Article hereof.

4. The charitable trust may not be liable for the acts which might have been committed by the trustees in violation of the provision laid down under Sub-Art. 1 of this Article hereof.

## 14. ፈቃድ ስለማሳደስ

1. በአዋጁ አንቀጽ 71 ስር የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው ፈቃድ ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ ከሚመለከተው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ዓመታዊ የሥራ ክንውንና የኦዲት ሪፖርቶች ጋር ከዚህ በታች የተመለከቱትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡-
   - ሀ) የሶስት ቀጣይ ዓመታት የበጀት ዕቅድ፤
   - ለ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ከሚመለከተው የመንግስት አስፈጻሚ አካል ጋር የገባው የፕሮጀክት ስምምነት ካለ የዚሁ ኮፒ፤ እና
   - ሐ) ቢሮው የሚጠይቃቸው ሌሎች ተጨማሪ ሰነዶች፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈቃድ ለማሳደስ የሚቀርበው ማመልከቻ አግባብ ባለው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሥራ መሪ የተፈረመና በውስጡ የያዛቸው መረጃዎች እውነት ስለመሆናቸው ማረጋገጫ የተሰጠበት መሆን ይኖርበታል፡፡ ለዕድሳቱ የሚፈጸመው የአገልግሎት ክፍያም ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተው ይሆናል፡

## 14. Renewal of License

1. Without prejudice to the provisions specified under Art. 71 of the Proclamation, an application for the renewal of license shall, together with annual working performance and audit reports of the charity or society, include such types of information as are indicated here below:
   - A a financial plan running for the following three fiscal years;
   - B a copy of the project agreement which the charity society may have concluded with the government executive organ concerned, if any; and
   - C other additional documents as may be requested for by the Bureau.
2. The application to be submitted for the renewal of license pursuant to sub.Art.1 of this Article hereof shall be signed by the pertinent officer of the charity or society and duly verified that the information contained therein is true. The service charge to be effected for such renewal shall be that indicated in the schedule annexed to this regulation.

3. ቢሮው የዕድሳት ጥያቄውን ያልተቀበለው እንደሆነ ምክንያቶችን ገልጾ ማመልከቻው ውድቅ መደረጉን ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

4. ቢሮው የዕድሳት ጥያቄውን አስመልክቶ በመፍቀድም ሆነ በመከልከል የሚሰጠው ማናቸውም ውሳኔ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መዝገብ ውስጥ ይመዘገባል፡፡

## 15. ስያሜን፣ የሥራ ቦታን ወይም መተዳደሪያ ደንብን ስለመለወጥ ወይም ስለማሻሻል

1. ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በአዋጁ አንቀጽ 68 መሠረት ስያሜውን የለወጠ ወይም መተዳደሪያ ደንቡን ያሻሻለ እንደሆነ ለውጡን ወይም ማሻሻያውን በሥራ ላይ ከማዋሉ በፊት ለቢሮው ማቅረብና ማስመዝገብ አለበት፡፡

2. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በአዋጁ አንቀጽ 68 መሠረት የሥራ ቦታውን የለወጠ እንደሆነ ለውጡን በአሥራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለቢሮው በጽሁፍ በማቅረብ ማስመዝገብ ይኖርበታል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርበው የምዝገባ ጥያቄ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የበላይ አካል ውሳኔ የያዘ ቃለ ጉባኤ እና ለመለወጥ

3. Where the Bureau has rejected the request for the renewal, it shall notify such rejection to the applicant in writing having stated grounds justifying its action thereof.

4. Any decision to be rendered by the Bureau by way of either granting or rejecting of the application for renewal shall be recorded in the register of charities and societies.

## 15. Alteration or Amendment of Designation, Place of Work or Rules

1. Where any charity or society has altered its name or amended its rule in accordance with Art. 68 of the proclamation, it shall submit such alteration or amendment to the Bureau and cause its registration thereof prior to its implementation of same.

2. Where any charity or society has changed its place of work in accordance with Art. 68 of the proclamation, it shall submit such change to the Bureau in writing within fifteen working days and cause the registration thereof.

3. The application for registration to be submitted pursuant to Sub-Art.1 of this Article hereof shall be accompanied by the minute containing the decision of the superior

ወይም ለማሻሻል የተፈለገው ስያሜ ወይም መተዳደሪያ ደንብ ቅጂ ማካተት ይኖርበታል፡፡

organ of the charity or society and the copy of name or rule proposed to be altered or amended thereof.

4. የስያሜውን ወይም የመተዳደሪያ ደንቡን ማሻሻያ በቢሮው ለማስመዝገብ የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ መጠን ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተው ይሆናል፡፡

4. The amount of service charge to be paid for the registration by the Bureau of the change of the name or amendment of the rule shall be the one as are prescribed in the Schedule annexed to the Regulation.

5. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ እንዲመዘገብለት የጠየቀው የስያሜ ወይም የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ ወይም በሌላ ሕግ ያልተከለከለ ከሆነ ለውጡ ወይም ማሻሻያው ተመዝግቦ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መዝገብ እንዲሰፍር ይደረጋል፡፡

5. Where the proposed change or amendments of name or rules of the charity or society are not prohibited by the Proclamation, this Regulation or by other laws, the said change or amendment shall be entered in the register of charities or societies.

6. ቢሮው የቀረበለትን የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ተቀብሎ ሲመዘግብ የተሻሻለውን ደንብ ለበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በማህተም አረጋግጦ ይሰጣል፡፡

6. Where the Bureau has accepted and registered the proposed amendment of the rule, it shall render such an amended rule to the charity or society, having same approved and certified with an official seal,

7. ቢሮው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ እንዲመዘገብለት ያቀረበውን የስያሜ ወይም የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ጥያቄ ያልተቀበለው እንደሆነ ማመልከቻው ተቀባይነት ያላገኘበትን ምክንያት ገልጾ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

7. Where the Bureau has rejected the request for the registration of amendment of name or rules of the charity or society, it shall notify same to the applicant in writing having stated the grounds for the action thereof.

## 16. ስለመዋሐድና መከፋፈል

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ለመዋሀድ ወይም ለመከፋፈል ሲወስን ጉዳዩን ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር ለቢሮው ማቅረብ ይኖርበታል፡-

   ሀ) አግባብነት ባለው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ የበላይ አካል የመዋሐድ ወይም የመከፋፈል ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፤

   ለ) የተከፋፈሉትን ወይም የተዋሃዱትን የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ዝርዝር፤

   ሐ) በውህደቱ ወይም በክፍፍሉ ውሳኔ ስለሚተላለፉት መብቶች እና ግዴታዎች ዓይነትና መጠን የተደረገ ስምምነት፤

   መ) ውሳኔው በተለይ መከፋፈልን የሚመለከት ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የንብረት ክፍፍሉ አፈጻጸም፤ እና

   ሠ) ቢሮው የሚጠይቃቸው ሌሎች ዝርዝሮች፡፡

2. መዋሐድን ወይም መከፋፈልን አስመልክቶ ቀደም ሲል የተደረገ ምዝገባ ቢኖር ውሳኔው አግባብ ባላቸው ህጎችና በበጎ አድራጎቱ ወይም በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተሰጠ ስለመሆኑ በቢሮው የተረጋገጠ እንደሆነ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተው የመደበኛ ምዝገባ ክፍያ ከተከፈለ በኋላ በአዲስ ሁኔታ

## 16. Merger and Division

1. Where any charity or society has decided to merge or divide, it shall submit the issue to the Bureau along with the following information:

   A. Evidence showing that a decision has been rendered by the superior body of the charity or society to that effect;

   B. the list of charities or societies which have been divided or merged thereof ;

   C. an agreement made as to the type and degree of the rights and obligations to be transferred by the decision introducing such division or merger;

   D. in case of division, the procedure for distribution of property; and

   E. other details to be specified by the Bureau.

2. In case of prior registration involving merger or division, where it is ascertained by the Bureau that the decision was rendered in accordance with the relevant laws and the rule of the charity or society, such shall be re-registered and published in a news paper having been adjusted to meet the new

ተስተካክሎ እንደገና እንዲመዘገብና በጋዜጣ እንዲታተም ይደረጋል፡፡

condition, following payment of the normal registration charge prescribed in the schedule annexed with this regulation.

## 17. በጋዜጣ ስለማሳተም

1. ቢሮው የተመዘገቡ፣ የታገዱ፣ የተሰረዙ እና የፈረሱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ዝርዝር ቢያንስ በስድስት ወር አንድ ጊዜ በጋዜጣ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ እደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው የተመዘገቡ፣ የፈረሱና የታገዱ በጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን ዝርዝር በየወሩ በሌሎች የመገናኛ ዜዴዎች ለሚመለከታቸው ክፍሎች ሊያሳውቅ ይችላል፡፡
3. የታገዱ፣ የተሠረዙ እና የፈረሱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን እና ማህበራትን ዝርዝር በጋዜጣ ለማውጣት የሚያስፈልገውን የማሳተሚያ ወጪ ቢሮው ይሸፍናል፡፡
4. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ቢኖርም የመፍረሱ ውሳኔ ላይ የተደረሰው በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም በማህበሩ ጠያቂነት የሆነ እንደሆነ የጋዜጣ ማሳተሚያ ወጪው የሚሸፈነው በድርጅቱ ወይም በማህበሩ አማካኝነት ይሆናል፡፡

## 17. Publication in a News Paper

1. The Bureau shall cause the publication of the list of those registered, suspended, revoked and dissolved charities and societies in a gazette at least once in six months.
2. Without prejudice to the provision of Sub-Art.1 of this Article hereof, the Bureau may notify to the departments concerned the list of those registered, suspended, revoked and dissolved charities and societies each and every month using other mass Medias.
3. The Bureau shall cover the cost required for the publication of the list of those suspended, revoked and dissolved charities and societies in a news paper.
4. Notwithstanding the provision of Sub-Art. 3 of this Article hereof, where the decision of dissolution has been arrived at upon the initiation of the charity or society, the expense for the publication of such fact in a news paper shall be born on the part of the charity or society itself.

5. ቢሮው ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሚያስመዘግበውን የስም ለውጥ ወይም ማሻሻያ ለውጡ ወይም ማሻሻያው በሚመዘገብበት ወቅት በጋዜጣ ማውጣት ይኖርበታል፡፡

6. ማንኛውም ለስም ለውጥ ወይም ማሻሻያ ምዝገባ የሚያመለክት የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከመደበኛው የምዝገባ ክፍያ በተጨማሪ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን የጋዜጣ ማሳተሚያ ክፍያ መክፈል ይኖርበታል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ስር የተመለከቱትን ጉዳዮች ቢሮው በሚወስነው ማናቸውም የመንግስት ጋዜጣ ያወጣል ወይም እንዲወጡ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሶስት
## የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ማህበራት እና ኮሚቴዎች ስለሚቋቋሙባቸው ሁኔታዎችና መስፈርቶች፣

### 18. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ለማቋቋም መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች፣

1. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሰረት የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅትን ለማቋቋም የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት ይኖርባቸዋል፡-

5. The Bureau shall cause the publication in a newspaper the change or amendment of name which any charity or society may have submitted to it upon the registration of same.

6. Any charity or society applying for registration of change of name or amendment of same shall, in addition to the normal registration charge, pay for the publication of such fact in a newspaper as prescribed in the schedule annexed to this Regulation.

7. The Bureau shall publish or cause the publication of the matters specified under this Article in any government newspaper on its own determination.

## PART THREE
## CONDITIONS AND REQUIREMENTS FOR THE FORMATION OF CHARITIES, SOCIETIES AND COMMITTES

### 18. Requirements to be Fulfilled for the Formation of a Charitable Endowments

1. The following requirements shall, so as to form a charitable endowment, be fulfilled in accordance with the Proclamation and this regulation thereof:

ሀ. በአዋጁ አንቀጽ 63 ንዑስ አንቀፅ (3) መሠረት የተዘጋጀ የምዝገባ ማመልከቻ ቅጽ፣

ለ. የአንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ መሥራቾች መኖር፣

ሐ. የመሥራቹ/ቾች የሕይወት ታሪክ ቅጽ፣ የፓስፖርት መጠን ያለው ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወረቀት ወይም የፀና ፓስፖርት ቅጂና የነዚህኑ ዋናዎች ለማመሣከሪያነት፣

መ. መሥራቹ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ከሆነ የታደሰ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሰነድ፣

ሠ. አግባብ ባለዉ አካል የተረጋገጠ የድርጅቱ የስጦታ ውል፣

ረ. ድርጅቱን ለመመስረት የተሰጠው፡-

I. ገንዘብ ከሆነ የዚሁ መጠንና ገንዘቡ ለምስረታ በታሰበው የዘለቄታ በጐ አድራጐት ድርጅት ስም በዝግ ሒሳብ የተቀመጠ ስለመሆኑ የሚያሣይ የባንክ መግለጫ፣

II. ሌላ ማናቸውም ንብረት ከሆነ የንብረቱ ዝርዝር መግለጫና ስለዚሁ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ ህጋዊ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ፣

A. an application form prepared for the registration pursuant to Art.63 Sub. Art. 3 of the Proclamation;

B. existence of one or more founders;

C. the life history form, passport size photo graph, renewed Keble Identification Card or a copy of valid passport of the founders/s along with the original ones for the purpose verification;

D. where the founder is an institution acquiring a legal personality, a renewed certificate to that effect;

E. a contract of donation pertaining to the endowment and approved by the relevant organ;

F. the donation granted in view of establishing the endowment:

I. where it involves money, a bank statement as to its specific amount and showing that such money has already been deposited in a blocked account in the name of the endowment proposed to be formed;

II. Where it involves any other property, a detailed specification to that effect as well as a document of title.

ሰ. ድርጅቱን በበላይነት እንዲመሩና እንዲያስተዳድሩ በመሥራቹ የተሾሙ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ዝርዝርና ከሕይወት ታሪካቸው ቅፅ ጋር የሚያያዝ ሁለት ሁለት የፓስፖርት መጠን ያለው ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወረቀት ወይም የፀና ፓስፖርት ቅጂና ዋናውን ለማመሳከሪያነት፣

ሸ. በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 መሠረት የተዘጋጀ የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ወይም ቢሮው በአዋጁ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀፅ (5) መሠረት ያዘጋጀውን ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ፣

ቀ. ድርጅቱ ለትግበራ ያዘጋጀው የፕሮጀክት ፕሮፓዛል፣

2. በዚህ ደንብ መሰረት የሚሾሙ ወይም የሚሰየሙ የስራ አመራር ቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን አምስት (5) ዓመት ይሆናል፤ ሆኖም ማናቸውም የቦርድ አባል ከሁለት ተከታታይ ጊዜ በላይ ሊሰየም ወይም ሊሾም አይችልም፡፡

## 19. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ለማቋቋም መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች፣

በዚህ ደንብ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀፅ (1) (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ)፣ (ረ)፣ (ሸ)፣ እና (ቀ) ከተመለከቱት መስፈርቶች በተጨማሪ የአደራ በጐ አድራጐት

G. The list of managing board members appointed by the founder in order to direct and administer the endowment and two passport size photo graphs each to be attached to the forms of their life history, renewed Keble Identification Card or a copy of valid passport along with the original ones for the purpose of verification;

H. A rule of the endowment prepared pursuant to Art. 6 of this Regulation or model rule prepared by the Bureau pursuant to Art. 10 Sub-Art. 5 of the Proclamation;

I. a project proposal prepared by the endowment for the purpose of implementation;

2. The term of office of those managing board members to be appointed or designated in accordance with this regulation shall last five (5) years; provided, however, that no board member may be re-designated or re-appointed in the excess of two consecutive times;

## 19. Requirements to be Fulfilled for the Establishment of a Charitable Trust

The following requirements shall, in addition to the provisions specified under Art. 18 Sub-Art. 1 (A), (B), (C), (D), (F),

ድርጅት ለመመስረት የሚከተሉት መስፈርቶችም መሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1. በሚመለከተው አካል የተረጋገጠ የድርጅቱ የአደራ መስጫ ሰነድ፤ እና
2. ድርጅቱን በበላይነት እንዲመሩና እንዲያስተዳድሩ በመሥራቹ የተሾሙ የአደራ ጠባቂዎች አባላት ዝርዝር፣ ከሕይወት ታሪክ ቅፃቸው ጋር የሚያያዝ ሁለት ሁለት ፓስፖርት መጠን ያለው ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወረቀት ወይም የፀና ፓስፖርት ቅጂና ዋናውን ለማመሳከሪያነት፡፡

## 20. የዘለቄታና የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ለማቋቋም የሚያስፈልግ አነስተኛ የገንዘብ መጠን

1. የዘለቄታ ወይም የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅት ለማቋቋም የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ቢሮው ለዚሁ ዓላማ በመመሪያ የሚወስነውን አነስተኛ የገንዘብ መጠን በቅድሚያ ማስያዝ ይኖርበታል፡፡
2. ይኸው አነስተኛ የገንዘብ መጠን አመልካቹ ሕጋዊ ሰውነት እስኪያገኝ ድረስ ለምስረታ በታሰበው የዘለቄታ በጐ አድራጐት ድርጅት ወይም የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅት ስም ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ ባንክ በዝግ ሒሳብ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

(H) and (I), of this Regulation, be fulfilled so as to form a charitable trust:

1. a trusteeship granting document of the charity approved by the pertinent organ; and
2. The list of those members of trustees appointed by the founder so that they would manage and administer the charity, two passport size pieces photo graphs to be attached to the forms of their life history, renewed Kebele Identification Card or a copy of valid passport along with the original ones for the purpose of verification.

## 20. Minimum Amount of Funds Required for the Formation of Charitable Endowments and Charitable Trusts

1. Any person desiring to form a charitable endowment or charitable trust shall first avail the security of the minimum amounts of funds which the Bureau would determine in a directive for such purpose.
2. The minimum amount of funds hereof shall be deposited in a bank located in Ethiopia with a blocked account in the name of a charitable endowment or charitable trust proposed to be formed thereof until such time that the applicant will have acquired legal personality.

3. ገንዘቡ በባንክ ይቀመጥ ዘንድ መሥራቹ ወይም የመሥራቹ ሕጋዊ ወኪል ለመረጠው ባንክ ቢሮው የድጋፍ ደብዳቤ ይፅፍለታል፡፡

4. መሥራቹ ወይም የመሥራቹ ሕጋዊ ወኪልም ገንዘቡ በዝግ ሒሳብ የተቀመጠ ስለመሆኑ የሚገልጽ የባንክ ማረጋገጫ ሰነድ ለቢሮው ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

5. አመልካች የዘለቄታ በጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ ሕጋዊ የምዝገባ ሰርተፊኬት ካገኘ በኋላ በዝግ ሒሳብ የተቀመጠው ገንዘብ በቢሮው ትዕዛዝ እንዲለቀቅ እና በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

## 21. ለዘለቄታ ወይም ለአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ምስረታ ስለሚሰጥ ንብረት፣

1. ለዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ለአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ማቋቋሚያ የተሰጠ ማናቸውም ንብረት ዋጋ በቢሮውና በመሥራቹ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ የጋራ ሥምምነት በተመረጠ የንብረት ገማች ባለሙያ፣ ህጋዊ የንብረት ግመታ ስራዎችን በሚያስፈጽሙ መንግስታዊ ተቋማት ወይም ጉዳዩ በሚመለከታቸው ሌሎች ህጋዊያን አካላት አማካኝነት በወቅቱ የገበያ ዋጋ በገንዘብ

3. The Bureau shall write a supporting letter to the bank preferred by the founder or his legal representative that might be required for the deposit of money.

4. The founder or his legal representative shall submit to the Bureau a statement of the bank showing that such money has been deposited in a blocked account.

5. The money deposited in the blocked account shall be made to be withdrawn by the instruction of the Bureau and implemented thereof following the acquisition of legal personality by the charitable endowment or charitable trust as per its applicant once it has fulfilled the necessary requirements.

## 21. Property Donated for the Formation of Charitable Endowment or Charitable Trust

1. The value of any property donated for the establishment of a charitable endowment or charitable trust shall be assessed in monitory terms having due regard to the current market price by the property valuation expert chosen through a joint agreement of the Bureau and the founder or his legal representative, by those government institutions in charge of executing lawful property assessment duties or by

ተተምኖ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ግምቱ ቢሮው የዘለቄታ ወይም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅትን ለማቋቋም በመመሪያ ከሚወስነው አነስተኛ የገንዘብ መጠን ማነስ የለበትም፡፡

2. ንብረቱ የመሥራቹ ሕጋዊ ሀብትና ከማናቸውም ዓይነት ዕዳም ሆነ ዕገዳ ነፃ ስለመሆኑ አግባብ ባለው አካል መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

other legal bodies pertaining thereto and its results submitted thereto; provided, however, that its estimated value may not be less than the minimum amount of funds which the Bureau is bound to determine in a directive for the formation of such endowment or trust.

2. It must be established on the part of appropriate body that such property is the lawful asset of the founder and free from any sort of liabilities or attachments.

## 22. የበጎ አድራጎት ተቋም ለመመስረት መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች፣

በአዋጁ አንቀጽ 63 ንኡስ አንቀፅ (3) መሠረት የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው የበጐ አድራጐት ተቋምን ለማቋቋም የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1. በቢሮው የተዘጋጀ የበጐ አድራጐት ተቋሙ የምዝገባ ማመልከቻ፣
2. ሶስትና ከዚያ በላይ የሆኑ መሥራቾች ዝርዝር፣ የእየአንዳንዳቸው ሁለት ጉርድ ፎቶግራፎች፣ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወረቀት ወይም የፀና ፓስፖርት ቅጅና ዋናዎቹ ለማመሳከሪያነት፣
3. መሥራቹ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም የሆነ እንደሆነ የዚሁ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣

## 22. Requirements to be fulfilled for the Formation of a Charitable Institution

Without prejudice to the provisions specified under Art. 63 Sub-Art. 3 of the Proclamation, the following requirements shall, so as to form a charitable institution, be fulfilled:

1. an application form for the registration of the charitable institution prepared by the Bureau;
2. The list of three and above, two pieces photo graphs, a renewed Kebele identification card or a copy of valid passport each and the original ones for the purpose of verification;
3. Where the founder is an institution having acquired legal personality, a certificate to that effect;

4. የተቋሙ መተዳደሪያ ደንብ ወይም ለዚሁ ዓላማ በቢሮው የተዘጋጀውን ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ መጠቀም ካስፈለገ የዚሁ አንድ ቅጅና በመስራቾች የተፈረመ የስምምነት ቃለ ጉባኤ፣
5. ለትግበራ የተዘጋጀ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል፣
6. መሥራቾች ተቋሙን ለመመስረት የሚያስይዙት፡-
   ሀ. ገንዘብ ከሆነ የዚሁ መጠንና ገንዘቡ በዝግ ሒሳብ የተቀመጠ ስለመሆኑ የሚያሣይ የባንክ መግለጫ እና
   ለ. ሌላ ማናቸውም ንብረት ከሆነ የንብረቱ ዓይነትና የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ፣

## 23. የበጎ አድራጎት ተቋምን ለመመስረት ስለሚያስፈልገው አነስተኛ የዋስትና ገንዘብ መጠን

1. የበጎ አድራጎት ተቋምን ለማቋቋም የሚፈልጉ መሥራቾች ቢሮው በመመሪያ የሚወስነውን አነስተኛ የገንዘብ መጠን ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ ባንክ በዋስትና መልክ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

4. rule of the institution or where required to utilize model rule prepared by the Bureau for the purpose, one copy of such document and the minute of the agreement duly signed by the founders;
5. a project proposal prepared for the purpose of implementation;
6. the guarantee which the founders have secured in view of establishing the institution:
   A. where it involves money, bank statement as its specific amount and showing that such money has already been deposited in a blocked account and;
   B. where it involves any other property, a type of specification to that effect as well as a document of title.

## 23. Minimum Amount of Security Fund Required for the Establishment of a Charity Institution

1. Those founders desiring to form a charitable institution shall avail the minimum amount of funds which the Bureau would determine through a directive in the form of security in a bank located in Ethiopia.

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተው ገንዘብ የተቋሙ ሕጋዊ ሰውነት ተጠብቆ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ በዝግ ሒሳብ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

3. ከዚህ በላይ የተመለከተውን ገንዘብ በዝግ ሒሳብ ለማስቀመጥ ይቻላቸው ዘንድ መሥራቾች ለቢሮው ሲያመለክቱ እነርሱ ለመረጡት ባንክ የድጋፍ ደብዳቤ ይፃፍላቸዋል፡፡

4. መሥራቾች የተባለው ገንዘብ በዝግ ሒሳብ የተቀመጠ ስለመሆኑ የሚገልጽ የባንክ ማረጋገጫ ሰነድ ለቢሮው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ገንዘቡንም ያለቢሮው የጽሑፍ ፈቃድ ከባንክ ማውጣት አይቻላቸውም፡፡

## 24. ለበጎ አድራጎት ተቋም ምስረታ በዋስትና ስለሚያዝ ንብረት

1. ለበጎ አድራጎት ድርጅት ተቋም መመስረቻ የተሰጠ ማናቸውም ንብረት ዋጋ በቢሮውና በመሥራቹ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ የጋራ ሥምምነት በተመረጠ የንብረት ገማች ባለሙያ፣ ህጋዊ የንብረት ግመታ ስራዎችን በሚያስፈጽሙ መንግስታዊ ተቋማት ወይም ጉዳዩ በሚመለከታቸው ሌሎች ህጋዊያን አካላት አማካኝነት በወቅቱ የገበያ ዋጋ በገንዘብ ተተምኖ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም

2. The fund specified under Sub-Art. 1 of this Article hereof shall remain having been deposited in a blocked account until so long as the legal personality of the institution has been maintained.

3. Where the founders apply to the Bureau so that they would be able to deposit the money specified here above in a blocked account, a supporting letter shall be written in their favor to the bank of their preference for such purpose.

4. The founders shall submit to the Bureau a bank statement showing the said money has been deposited in a blocked account; provided, ,however, that they may not be able to withdraw such money from the bank without the written permission of the Bureau.

## 24. Property Held in the Form of Security for the Formation of a Charitable Institution

1. The value of any property donated for the establishment of a charitable institution shall be assessed in monitory terms having due regard to the current market price by the property valuation expert chosen through a joint agreement of the Bureau and the founder or his legal representative, by those government institutions in charge of executing lawful property assessment duties or by other legal bodies

ግምቱ ቢሮው የበጎ አድራጎት ተቋም ለማቋቋም በመመሪያ ከሚወስነው አነስተኛ የዋስትና ገንዘብ መጠን ማነስ የለበትም፡፡

2. ንብረቱ ከማናቸውም ዓይነት ዕዳም ሆነ ዕገዳ ነፃ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ሰነድ አግባብ ካለው አካል መቅረብ ይኖርበታል፡፡

3. አግባብ ባለዉ አካል ተረጋግጦ የተሰጠው ዋናው የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ በቢሮው ተጠብቆ ይቆያል፡፡

4. ንብረቱ ሊበላሽ ወይም ዋጋው ሊቀንስ ይችላል ወይም ለማስተዳደር ያስቸግራል ተብሎ የተገመተ እንደሆነ በቢሮውና በመሥራቾቹ ሥምምነት በወቅቱ የገበያ ዋጋ ተሸጦ ገንዘቡ በዝግ ሒሳብ በበጎ አድራጎት ተቋሙ ሥም እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

5. በዝግ ሒሳብ የተቀመጠውን ገንዘብ ያለቢሮው የጽሑፍ ፈቃድ ማውጣት አይቻልም፡፡

pertaining thereto and its results submitted thereto; provided, however, that its estimated value may not be less than the minimum amount of security funds which the Bureau is bound to determine in a directive for the formation of such a charitable institution.

2. A document which would ascertain that the property is free from any sort of liabilities or attachments must be submitted thereto on the part of the appropriate body.

3. The original document of title rendered following its certification by the appropriate body shall be maintained with the Bureau.

4. Where it has been assumed that the property might be spoiled or undervalued or be difficult to administer, it shall be sold at the current market price with a joint agreement between the Bureau and the founder and the money therefrom shall be caused to be deposited in a blocked account in the name of the charitable institution.

5. It may not be possible to withdraw from the bank the money deposited in the blocked account without the written permission of the Bureau.

## 25. የበጎ አድራጎት ማህበር ለማቋቋም መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች፣

1. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሰረት የበጎ አድራጎት ማህበር ማቋቋም የሚችሉት በዜግነት ኢትዮጵያዊያን የሆኑ፣ ዕድሜያቸው አስራ ስምንት ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፣ በቁጥር ከአስራ አንድ ያላነሱና ችሎታቸው በህግ ወይም በፍርድ ውሳኔ ያልተገደበ የተፈጥሮ ሰዎች መሆን ይኖርባቸዋል፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተጠቀሰው ድንጋጌ ቢኖርም የሚቋቋመው የበጎ አድራጎት ማህበር ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች በአባልነት ያሉበት ማህበር ሆኖ የሚቋቋም ከሆነ ቁጥራቸው ከአስራ አንድ በታች ቢሆንም የበጎ አድራጎት ማህበር ሆነው እንዲቋቋሙ ቢሮው ሊፈቅድ ይችላል፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው የበጎ አድራጎት ማህበር ለማቋቋም የሚቀርበው ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ (1) ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ) እና (ረ) ከተደነገጉት በተጨማሪ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡-

## 25. Requirements to Be Fulfilled for the Formation of a Charitable Society

1. Those who would be able to form a charitable society in pursuance of the Proclamation and this regulation shall be natural persons who are Ethiopians by citizenship, eighteen years old and above by age, not less than eleven by number and not interdicted by law or judicial decision;

2. Notwithstanding the provision of Sub-Art. 1 of this Article hereof, where a charitable society in view to be constituted out of the union of other organizations having acquired legal personality as individual member thereof, the Bureau may allow them to unit and be established as one charitable society even though their number might be less than eleven.

3. Without prejudice to the provisions specified under Sub-Arts.1 and 2 of this Article hereof, an application to be submitted for the formation of a charitable society shall, in addition to those specified under Art.4 Sub.Art.1 letter number A, B, C, D, and F of this Regulation, include the following information:

ሀ) በመስራቾች የተፈረመ የማህበሩ መመስረቻ ቃለ ጉባኤ፣

ለ. የበጎ አድራጎት ማህበሩን የሥራ መሪዎች ማንነት የሚገልፅ የሕይወት ታሪክ ቅፅ፣ የእየአንዳንዳቸው ሁለት የፓስፖርት መጠን ያለው ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወረቀት ወይም የፀና ፓስፖርት ቅጂና ዋናው ለማመሳከሪያነት፣

ሐ. ማህበሩ ሊያከናውን ያሰበው የሥራ ዕቅድ እና የበጀት ኘሮፖዛል፣ እና

መ. ቢሮው አስፈላጊ ናቸው ብሎ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች ጉዳዮች፡፡

## 26. የበጎ አድራጎት ኮሚቴ ለማቋቋም መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች፡-

1. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሰረት የበጐ አድራጐት ኮሚቴ ሊያቋቁሙ የሚችሉት በዜግነት ኢትዮጵያዊያን የሆኑ ወይም በትውልድ ኢትዮጵያዊያን የሆኑና በኢትዮጵያ ውስጥ የመኖሪያ ፈቃድ ያላቸው፣ ዕድሜያቸው አስራ ስምንት ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፣ ቁጥራቸው ከአምስት ያላነሰ ሆኖ ችሎታቸው በህግ ወይም በፍርድ ውሳኔ ያልተገደበ የተፈጥሮ ሰዎች ይሆናሉ፡፡

A. a minute establishment of the charitable society duly signed by the founders;

B. life history form identifying the managing officers of the charitable society, two passport size pieces of photo graphs each, renewed Kebele Identification Card or a copy of valid passport along with the original ones for the purpose of verification;

C. work and budget proposal intended to be undertaken by society ; and

D. other particulars which the Bureau would determine in a directive, as might be necessary.

## 26. Requirements to Be Fulfilled for the Establishment of Charitable Committee

1. Those who may be able to form a charitable committee in pursuance of the proclamation and this regulation are natural persons who are Ethiopians by citizenship or ethnic Ethiopians holding a residence permit in Ethiopia as well as eighteen years old and above by age, not less than five by number and not interdicted by law or judicial decision;

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) ስር የተመለከተዉ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የበጐ አድራጐት ኮሚቴን በቢሮው ለማስጸደቅ የሚቀርበው ማመልከቻ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡-

   ሀ. የኮሚቴው መለያ ሥም እና ዋና አድራሻ፣

   ለ. ኮሚቴው የተቋቋመበት ዓላማ/ዎች

   ሐ. ኮሚቴው ሊሰበስበው ያቀደው የገንዘብ ወይም የንብረት መጠን፣

   መ. የኮሚቴው የገንዘብ ምንጭ እንዲሁም ከሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ የሚያሳይ መግለጫ፣

   ሠ. ኮሚቴው ሊያከናውን ያሰበው የሥራና የበጀት ዕቅድ፣

   ረ. በመስራቾች የተፈረመ የኮሚቴው ምስረታ ቃለ-ጉባዔ፣

   ሰ. የኮሚቴውን የሥራ መሪዎች ማንነት የሚገልጽ የህይወት ታሪክ ቅጽ፣ የፓስፖርት መጠን ያለው የእያንዳንዳቸው ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወረቀት ወይም የፀና ፓስፖርት ቅጅ ዋናው ለማመሳከሪያነት፣

2. Without prejudice to the provision specified under Sub-Art.1 of this Article hereof, an application to be submitted for the Bureau in order to obtain the approval of a charitable committee shall contain the following information:

   A. the identifying name and the principal address of the committee;

   B. objective/s for the establishment of the committee;

   C. the amount of funds or property proposed to be collected by the committee;

   D. the committee's source of finance together with a statement showing of its domestic proportion vis-a-vis the external one in percent;

   E. work and budget plan intended to be undertaken by the committee;

   F. a minute for the establishment of the committee duly signed by the founders;

   G. life history forms identifying the managing officers of the committee, a passport size piece of photo graph each, renewed Kebele Identification Card or a copy of valid passport along with the original ones for the purpose of verification;

ሸ. የኮሚቴው አደረጃጀት፣ የአመራር አባላቱ ሥልጣንና ተግባር፣ እንዲሁም የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት፣

ቀ. ኮሚቴው በሥራ ላይ የሚቆይበት ጊዜ፣

በ. ኮሚቴው የተፈቀደለት ጊዜ ሲያበቃ ንብረቱ ወይም ገንዘቡ ሊተላለፍለት የታሰበ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም የመንግስት አካል ቢኖር ይሄንኑ የሚያመለክት መግለጫ፣

ተ. ኮሚቴው ገንዘብ ወይም ንብረት የሚያሰባስብበት ስፍራና የአሰባሰብ ዘዴ፣

ቸ. ኮሚቴው ዓላማውን/ዎቹን ለማሳካት የማይበቃ ገንዘብ ወይም ንብረት የሰበሰበ እንደሆነ ወይም የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት ዓላማውን/ዎቹን ለማሳካት ከሚፈልገው በላይ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ሥራ ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ የሚያሳይ መግለጫ፣

ኀ. ቢሮው በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች ጉዳዮች፡፡

H. structure of the committee as well as powers and duties of its leadership members, and meeting and decision making procedures;

I. duration of the committee on duty;

J. Where the effective duration validly allowed for the committee expires, a statement indicative of a charitable organization or government body to which its property or funds is intended to be transferred, if any;

K. place in which the committee would collect funds or property and the method of collection thereof;

L. Where the committee has collected fund or property which is not sufficient enough to achieve its objective/s or the funds or property collected thereof is found to be in excess the amount needed for accomplishment of its objective/s, a statement showing the condition in which such funds or property might be put use,

M. other matters to be determined in a directive by the Bureau.

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 (ለ) መሰረት ኮሚቴው የሚሰማራባቸው የበጐ አድራጐት ዓላማዎች በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ-ቀ) ስር የተዘረዘሩት ብቻ ይሆናሉ፡፡

3. The charitable committee's objectives in which a charitable committee is to be engaged pursuant to Sub-Art. 2 (B) of this Article hereof shall be only those specified under Art. 7 Sub-Art. 1 (A) through (I) of the Proclamation.

## ክፍል አራት
## ሪፖርቶች እና መረጃዎች

## PART FOUR
## REPORTS AND INFORMSTION

### 27. ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ

1. በአዋጁ አንቀጽ 73 መሠረት የሚዘጋጅ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ የሚከተሉትን ዝርዝሮች ሊይዝ ይገባል፡-
   ሀ. በበጀት ዓመቱ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን ገቢ እና ወጪ የሚያሳይ የሒሳብ መግለጫ፣
   ለ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የገቢ ምንጭ በተለይም ከውጭ የተገኘ ገቢ እና የአስተዳደርና የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ ድርሻ ማብራሪያ፤
   ሐ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በአመቱ መጨረሻ ላይ ያለውን አጠቃላይ ሀብት፣ ዕዳ እና ካፒታል የሚያሳይ የሃብት ሚዛን መግለጫ፤

### 27. Annual Statement of Accounts

1. An annual statements of accounts to be prepared in accordance with Art.73 of the Proclamation shall contain the following particulars:
   A. an income and expenditure account showing the income and expenditure of the charity or society during the budget year;
   B. an explanation of the source of the income specially in relation to income from forein sources and the ratio of administrative and operational costs of the charity or society;
   C. a balance sheet showing the assets, liabilities and capital of the charity or society at the end of the financial year;

መ. የሂሳብ መግለጫውን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ የዋለውን የሂሳብ አሰራር መግለጫ እና

ረ. ሌሎች ቢሮው በመመሪያ የሚወስናቸው ዝርዝሮች፡፡

2. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከማናቸውም ምንጭ የሚያገኙትን ገቢ እንዲሁም የአስተዳደርና የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ ማስላትን የሚመለከቱ ዝርዝር መመሪያዎችን ቢሮው ያወጣል፡፡

## 28. ዓመታዊ የሂሳብ ምርመራ

በአዋጁ አንቀጽ 74 መሠረት የሚዘጋጅ ዓመታዊ የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ ይኖርበታል፡-

ሀ. የሂሳብ መዛግብቱና መግለጫው የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን የገንዘብ እንቅስቃሴ እና ያለበትን ሁኔታ በሚገባ የሚያሳይ ሆኖ መገኘት፣

ለ. መዛግብትን ጨምሮ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን አጠቃላይ ሃብት፣ የሂሳብና ሌሎች መዛግብትን በአግባቡ መያዙን፤

ሐ. የሂሳብ መዛግብቱና መግለጫው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ከውጭ የሚያገኘውን ገቢ ለይቶ በሚያሳይ መልኩ መቀመጡን፤

D. an explanation of accounting procedure used to prepare the accounts; and

E. other particulars to be determined in a directive by the Bureau.

2. The Bureau shall issue specific guidelines on how to calculate the income and expenditure of charities and societies in relation to income from any sources and administrative and operational costs.

## 28. Annual Auditing of Accounts

The report of the annual auditing of accounts to be prepared in accordance with Art.74 of the Proclamation shall contain the following particulars:

A. whether the account records and statement fairly show the financial transactions and stase of affairs of the carity or sicety;

B. whether it properly keeps the accounts and other records, including the records of all entire asset of the charity or society are properly kept thereof;

C. whether the account records and statement kept in such a way as to specifically show the income which the charity or society would generate from foreign sources;

መ. ኦዲተሩ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሌሎች ዝርዝሮች፤ እና

ሠ. ቢሮው በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች ዝርዝሮች፡፡

## 29. ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት

1. በአዋጁ አንቀጽ 75 መሠረት የሚዘጋጀው ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ ይኖርበታል፡-

ሀ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ዓላማው/ዎቹን ለማሳካት የቀረጻቸው የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅዶች እንዲሁም ሲኖረው ዓመታዊ ፖሊሲና ስትራቴጅ፤

ለ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ያከናወናቸው ተግባራት ማጠቃለያና የነዚሁ አጠቃላይ ግምገማ፤

ሐ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሚፈፅማቸው ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ዝርዝር፤

መ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በወቅቱ ያለውን ሃብት፣ ሊያውል ያቀደበትን ዓላማ ማብራሪያና እንዲሁም የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅዶቹን፤ እና

ሠ. ቢሮው በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች ዝርዝሮች፡፡

D. other details to be specified by the auditor as necessary; and

E. other particulars to be determined by a directive of the Bureau.

## 29. Annual Activity Report

1. The annual activity report to be prepared pursuant to Art. 75 of the Proclamation shall contain the following particulars:

A. short and long-term plans which the charity or society may have formulated in order to achieve its objective/s as well as the annual policy and strategy if it has any;

B. summary of activities which the charity or society has carried out in the outgoing budget year and along with general evaluation of same;

C. the list of those projects pending completion which the charity or society would implement thereof;

D. the asset currently held by the charity or society, the explanation of the purpose for which it is intended to be utilized as well as its short and long-term plans; and

E. other particulars which the Bureau would determine in a directive.

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም የብዙሃን ማህበራት ለቢሮው የሥራ ክንውን ሪፖርት እንዲያቀርቡ አይገደዱም፡፡

3. በቂና አሳማኝ ምክንያት ሳይኖረው ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በበጀት ዓመቱ ውስጥ ዓላማውን ለመፈፀም የሚያስችል አንዳች ተግባር ሳያከናውን መቅረቱ የተረጋገጠ እንደሆነ በቢሮው በኩል የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤ በተከታዩ ዓመት ምንም ተግባር ካላከናወነ ደግሞ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

## 30. ስብሰባን ስላለማሳወቅ

1. የአዋጁ አንቀጽ 87 ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በአዋጁ አንቀጽ 81 መሠረት የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ከመካሄዱ ከሰባት የሥራ ቀናት አስቀድሞ የስብሰባውን ጊዜና ቦታ ሳያሳውቅ የቀረ ማናቸውም ድርጅት ወይም ማህበር የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊሆን አይችልም፡፡

2. Notwithstanding the provision what has been provided for under Sub-Art. 1 of this Article hereof, mass-based societies may not be obliged to submit activity reports to the Bureau;

3. Where is established that any charity or society has, save adequate and convincing cause, failed to carry out any such task as to accomplish its purpose within the outgoing budget year, it shall be served with a written warning on the part of the Bureau; provided that it may even be deprived of its license, should it continue doing nothing with the following year as well.

## 30. Failure to Notify Meeting

1. Without prejudice to the provisions specified under Art. 87 Sub-Art.1 of the Proclamation, any charity or society failing to notify the meeting time and place of its general assemble prior to seven working days of such meeting pursuant to Art.81 of the Proclamation may be served with a written warning.

2. The warning served in accordance with Sub-Art. 1 of this Article hereof may not be given more than once.

## 31. የባንክ ሂሳብ ስለመክፈትና ስለማሳወቅ

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የባንክ ሂሳብ ለመክፈት ለቢሮው ማሳወቅና የድጋፍ ደብዳቤ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

2. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በአዋጁ አንቀጽ 78 ስር በተደነገገው መሠረት ያሉትን የባንክ ሂሳቦች ከሚከተሉት ዝርዝሮች ጋር ለቢሮው ማሳወቅ አለበት፡-

   ሀ. የባንክ ሂሳቦች ብዛትና ዓይነት እንዲሁም የተከፈቱበት ባንክና የቅርንጫፉ ስም እና የባንክ ሂሳቦቹ መለያ ቁጥር፤

   ለ. የባንክ ሂሳቡ በማን እንደሚንቀሳቀስ፤

   ሐ. በየጊዜው የሚቀርብ የባንክ ሂሳብ መግለጫ፤

   መ. ቢሮው በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎች፡፡

3. በቢሮው የተመዘገበና በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀስ ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የባንክ ሂሳብ በራሱ ስም ሊከፍት የሚችለው በክልሉ ውስጥ በሚገኝ ባንክ ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 31. Opening and Notifying of Bank Accounts

1. Any charity or society shall notify to the Bureau and obtain a supporting letter in order to open a bank account.

2. Any charity or society shall, in accordance with what has been provided for under Art. 78 of the Proclamation, notify to the Bureau all the bank accounts in its possession along with the following particulars:

   A. number and type of bank accounts as well as the name of the bank and its branch in which such accounts are opened along with their respective identifying numbers;

   B. by whom such accounts are operated;

   C. a statement of account to be submitted periodically;

   D. other relevant details to be determined in a directive by the Bureau.

3. Any charity or society registered by the Bureau and operating within the territorial limit of the Region may be able to open a bank account in its name only in such bank located therein.

4. ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የባንክ ሂሳቡን ከዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርቱ ጋር ወይም ቢሮው በጽሁፍ በሚጠይቀው በማናቸውም ጊዜ ለቢሮው ማቅረብ አለበት፡፡

## 32. አባላትንና የሥራ መሪዎችን የሚመለከቱ መረጃዎች

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የአባላቱንና የሥራ መሪዎቹን ዝርዝር መረጃዎች መዝግቦ መያዝና እንዳስፈላጊነቱ ለቢሮው ማስተላለፍ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚያዘው መረጃ የሚከተሉትን ዝርዝሮች ማካተት ይኖርበታል፡-

   ሀ. የአባላት፣ የሥራ መሪዎችና የበላይ አካል አባላቱ ሙሉ ስም፣ ዕድሜ፣ ጾታ፣ ዜግነት፣ የመኖሪያ አድራሻና የትምህርት ደረጃ፣

   ለ. የሥራ መሪዎችና የበላይ አካል አባላቱ የስራ ድርሻ፣ የኃላፊነት ደረጃ እና የሥራ ቦታ፣

   ሐ. ቢሮው በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች መረጃዎች፡፡

3. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (2) (ለ) ስር የተጠቀሱትን መረጃዎች እና

4. A charity or society shall include its bank account with the annual activity repot submitted to the Bureau or present it at any time upon the request of the Bureau in writing.

## 32. Information regarding Members and Officers

1. Any charity or society shall register and maintain the detailed information of its members and officers as well as transfer same to the Bureau, as might be necessary.

2. The information kept in accordance with Sub-Art. 1 of this Article hereof shall include the following particulars:

   A. full name, age, sex, nationality, residential address and educational qualification of the members, officers and their superior;

   B. share of duty, degree of responsibilities and work place of officers and members of the superior organ;

   C. other details to be determined in a directive by the Bureau.

3. Any charity or society shall notify to the Bureau the information specified under Sub-Art. (2) (B) of this Article hereof and, as the case may be

እንደአግባብነቱ የአባላቱን ስም፣ ዕድሜና ጾታ ከዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርቱ ጋር ወይም ቢሮው በሚጠይቅበት በማንኛውም ጊዜ ለቢሮው ማሳወቅ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው ቢኖርም የብዙሃን ማህበራት ብዛታቸውን ከማሳወቅ በስተቀር የአባሎቻቸውን ዝርዝር መረጃ ለቢሮው ማቅረብ አያስፈልጋቸውም፡፡

5. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሥራ መሪውን ወይም የበላይ አካል አባሉን ሲለውጥ ይኸው በተደረገ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለውጡን ለቢሮው ማሳወቅ አለበት፡፡

6. ቢሮው ከማንኛውም በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር አባላቱን ወይም የሥራ መሪዎችን በሚመለከት የሚፈልገውን ዝርዝር መረጃ ሲጠይቅ በጽሁፍ መሆን አለበት፡፡

7. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በቢሮው የተፈለገውን ዝርዝር መረጃ ቢሮው በሚያስቀምጠው አግባብነት ባለው ጊዜ ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡

8. በአዋጁ አንቀጽ 87 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተውን ግዴታ

appropriate, the name, age and sex of its members together with its annual cavity report to be submitted thereof or at any time upon the request of the Bureau.

4. Notwithstanding the provision of Sub-Art. 3 of this Article hereof, mass-based societies may, with the exception of their numerical size, not be requested to provide to the Bureau detailed information regarding their membership.

5. Where any charity or society has changed its officer or member of its superior organ, it shall notify such change to the Bureau within one month from the date on which an action having been carried out.

6. Where the Bureau requests detailed information from any charity or society as regards the latter’s members or officers, it shall be done in writing.

7. Any charity or society shall submit detailed information required by the Bureau in an appropriate time to be set for the purpose.

8. Without prejudice to the provision specified under Art. 87 of the Proclamation, the Bureau may, having

ያላሟላን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በጊዜ ገደብ የተወሰነ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የተባለውን መረጃ እንዲያሟላ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ሆኖም የዚህ ዓይነቱ ማስጠንቀቂያ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊሰጥ አይችልም፡፡

given it a written warning in a specified time limit, cause a charity or society failing to fulfill the duty indicated under Sub-Art. 2 of this Article hereof to furnish the said information; provided, however, that such type of warning may not be issued more than once.

## ክፍል አምስት
## ስለገቢ ማስገኛ ሥራዎችና ህዝባዊ መዋጮ

## PART FIVE
## INCOME GENERATING ACTIVITIES AND PUBLIC COLLECTIONS

### ንዑስ ክፍል አንድ
### ስለገቢ ማስገኛ ሥራዎች

### SUB-PART ONE
### INCOME GERNERATING ACTIVITIES

**33. የገቢ ማስገኛ ሥራ ከዓላማ ጋር ተያያዥ ስለመሆኑ**

የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሚሰማራበት የገቢ ማስገኛ ስራ ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ከተቋቋመበት ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡ ዝርዝሩ ቢሮው ይህንን ደንብ ተከትሎ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**33. Relevance of Income Generating Activity with Objective**

Income generating activity in which a charity or society engages shall be related with the objective for which the charity or society has been established. Particulars shall be determined in a directive which the Bureau may issue following this Regulation.

## 34. በገቢ ማስገኛ ሥራ የተገኘ ገቢ ለዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ ብቻ ስለመዋሉ

1. ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በገቢ ማስገኛ ስራ ላይ ተሰማርቶ የሚያገኘው ገቢ ለድርጅቱ ወይም ለማህበሩ አስተዳደራዊ ወጪዎች መሸፈኛነት መዋል አይኖርበትም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተደነገገው ቢኖርም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ የገቢ ምንጭ ከገቢ ማስገኛ ተቋማት ብቻ የሚመነጭ በሚሆንበት ጊዜ ከገቢ ማስገኛ ስራ የተገኘን ገቢ ለአስተዳደራዊ ስራዎች ወጪ መጠቀምን የሚከለክል አይሆንም፡፡
3. በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም በማህበሩ ስር ያለ የአስተዳደር ስራ በገቢ ማስገኛው ውስጥም በተደራቢነት አገልግሎት የሚሰጥ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ወጪው የዋናው በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር አስተዳደራዊ ወጪ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
4. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ አስተዳደርና አስተዳደራዊ ወጪዎች ከገቢ ማስገኛ ስራው አስተዳደርና አስተዳደራዊ ወጪዎች መለየት ይኖርባቸዋል፡፡

## 34. Utilization of Income Obtained Through Income Generating Activity only for the Execution of the Objective

1. No income obtained by any charity or society upon engagement in an income generating activity may be utilized to cover its administrative costs.
2. Notwithstanding the provision of Sub-Art. 1 of this Article hereof, where the source of income of the charity or society is generated only from those income generating institutions, it may not prohibit the utilization of such an income for the activities of administrative cost.
3. Where an administrative activity is found to also include the provision to its income generating activity, such an expense shall be considered as constituting the principal administrative cost of such charity or society.
4. The administration and administrative cost of the charity or society shall be separated from the administration and administrative cost of its income generating activities.

## 35. ከገቢ ማስገኛ ሥራ የሚገኝ ትርፍ ለአባላት የማይከፋፈል ስለመሆኑ

1. ከገቢ ማስገኛ ስራዎች የሚገኝ ማናቸውም ገቢ ለአባላት ወይም ለተጠቃሚዎች በቀጥታ በገንዘብም ሆነ በቁስ ሊከፋፈል አይችልም፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ስር የተደነገገው ቢኖርም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከገቢ ማስገኛ ስራ የሚያገኘውን ገቢ ለአባላት ወይም ለተጠቃሚዎች ለሚሰጠው የበጐ አድራጐት አገልግሎት ከማዋል አይታገድም፡፡

## 36. በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ ለመሠማራት ስለሚያበቁ መመዘኛዎች

ቢሮው በገቢ ማስገኛ ስራ ላይ ለመሰማራት በሚቀርብ ማመልከቻ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡-

1. የታሰበው የገቢ ማስገኛ ስራ የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ከተመዘገበበት ዓላማና ከተሰማራበት የስራ መስክ ጋር ተያያዥነት ያለዉ መሆኑን፣
2. ለመሰማራት ጥያቄ የቀረበበት የገቢ ማስገኛ ስራ ከመልካም ስነ-ምግባር ጋር ተቃራኒ ያልሆነ መሆኑን፣

## 35. Non-Distribution Among Members of Profit Obtained from Income Generating Activities

1. Any income obtained from the income generating activities may not be directly distributed among members or beneficiaries in cash or in kind.
2. Notwithstandind the provision of Sub. Art. 1 of this Article hereof, no charity or society may be barred utilizing the income to be obtained from income generating activities for charitable services to be delivered for its members or beneficiaries thereof.

## 36. Requirements Qualifying to Engage in Income Generating Activities

The Bureau shall, While deciding on an application submitted for engagement in an income generating activities, take into account the following matters, :

1. Weather the intended income generating activity is related to the purpose for which the charity or society has been registered and the sectoral duty of its engagement;
2. Weather the income generating activity sought for an engagement is not contrary to good ethical conduct;

3. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሚሰማራበት የንግድ ዘርፍ የታወቀ መነሻ ካፒታል ያለው መሆኑን፣
4. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የቢዝነስ እቅድ አዘጋጅቶ ያቀረበ መሆኑን፡፡
5. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በአዋጁና በሌሎች ህጎች የተቀመጡ ግዴታዎችን አክብሮ በመሥራት ላይ ያለ መሆኑን፤

3. Weather the commercial sector in which the charity or society would engage has a recognized initial capital;
4. That the charity or society has prepared and submitted business its plan thereto.
5. Weather the charity or society is operating in observance of dutities laid down under the Proclamation and other laws;

## 37. ስለንግድ ሥራ ፈቃድና ሌሎች ሁኔታዎች

1. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሰረት ገቢ በሚያስገኙ ስራዎች ላይ ለመሰማራት የጠየቀ ማናቸውም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር ከቢሮው በፅሁፍ ፈቃድ ካገኘ በኋላ ትርፍ በሚያስገኙ ስራዎች ላይ ለመሰማራት የሚያስችለውን የንግድ ስራ ፈቃድ ከተገቢው አካል ማውጣት ይኖርበታል፡፡
2. አግባብ ያላቸው የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በንግድና ኢንቨስትመንት ወይም ትርፍ ለማግኘት በተቋቋሙ ሌሎች ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው የምዝገባ፣ የፈቃድ፣ የግብር እና ሌሎች ግዴታዎች በገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይም ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፡፡
3. የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የገቢ ማስገኛ ስራዎችን ለማከናወን ከንግድና ኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ

## 37. Business License and other Conditions

1. Any charity or society applying to engage in an income generating activity shall, after having obtained a written permit from the Bureau, acquire a business license enabling it to engage in profit making activities from the pertinent organ.
2. Without prejudice to the relevant provisions of this regulation hereof, the registration, licensing, taxation and other obligations to be imposed on business and investment or on those organizations established for profit shall be applicable, mutatis mutandis, to income generating activities.
3. The charity or society shall immediately notify to the Bureau any license certifications, tax identification number

በሌሎች ህጎች መሠረት የሚያገኛቸውን ማናቸውንም የፈቃድ ሰርተፍኬቶች፣ የግብር መለያ ቁጥርና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ወዲያውኑ ለቢሮው ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

4. የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ገቢ በሚያስገኝ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚያወጣው የንግድ ፈቃድም ሆነ የሚያገኛቸው ማናቸውም መብቶች ፀንተው የሚቆዩት የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ህጋዊ ሰውነቱ ተጠብቆ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ ብቻ ይሆናል፡፡

## 38. ስለስያሜ

1. የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በገቢ ማስገኛ ስራ የተሰማራበት የንግድ ስም ከበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ስም የተለየ መሆን ይኖርበታል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ስያሜን በሚመለከት አግባብነት ያላቸው የሀገሪቱ የንግድ ህግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## 39. ስለሂሳብ አያያዝና የገንዘብ አጠቃቀም

1. በገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ የተሰማራ ማናቸውም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር ገቢ የሚያስገኙ ስራዎችን በተመለከተ ከበጐ አድራጐት ስራው የተለየ የሂሳብ መዛግብት የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

and other related matters which it would obtain pursuant to other laws in relation to business and investment in order to undertake income generating activities.

4. The business license which the charity or society has acquired to engage in an income generating activity or any right it would enjoy therein shall be remain valid only until such time that the legal personality of the charity or society will have been maintained thereof.

## 38. Designation

1. The trade name in which the charity or society is engaged in an income generating activity shall be distinguished from that generally used by the charity or society.
2. Without prejudice to the provision of Sub-Art. 1 of this Article, the relevant provisions of the country's commercial code shall apply with regard to designation hereof.

## 39. Keeping of Accounts and Financial Utilization

1. Any charity or society which has been authorized engage in an income generating activity shall have the obligation to keep separate books of account with regard to income generating activities as distinct from its charitable ones.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የገቢ ማስገኛ ስራዎችን በተመለከተ የሚያዘው የሂሳብ መዝገብ በንግድ፣ ኢንቨስትመንት እና በግብር ህጐች ውስጥ የተዘረዘሩትን የሂሳብ አያያዝ መስፈርቶች ያሟላ መሆን ይኖርበታል፡፡
3. የገቢ ማስገኛ ስራው ሂሳብ ከበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሂሳብ የተለየ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. የገቢ ማስገኛ ስራዎችን አስመልክቶ የባንክ ሂሳብ መክፈት የሚቻለው ይህንኑ ለቢሮው በቅድሚያ በማሳወቅና ፈቃድ በማግኘት ይሆናል፡፡
5. የገቢ ማስገኛ ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችለው የምዝገባ ጉዳይ ማስፈፀሚያ ወጭና ለስራው ማስጀመሪያ የሚውለው ካፒታል በበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሚሸፈን ይሆናል፡፡
6. የገቢ ማስገኛ ተቋሙ ስራ ከጀመረ በኋላ የሚካሄዱት ማናቸውም አይነት የገንዘብ እንቅስቃሴዎች ከበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ገንዘብ-ነክ እንቅስቃሴዎች ጋር ግንኙነት አይኖራቸውም፡፡

2. The maintenance of books carried in accordance with Sub-Art. 1 of this Article hereof as regards the income generating activity shall fulfill those requirements pertaining to the keeping of accounting records laid down under of business, investment and tax laws.
3. The accounts belonging to the income generating activity shall be distinct from those accounts of the charity or society.
4. It shall be through prior notification to the Bureau and acquisition of that it would be possible to open a bank account for purpose of income generating activities.
5. The expenses incurred for the registration affairs with regard to the carrying out of the income generating activity and the capital to be invested for the commencement of task shall be covered by f the charity or society.
6. All types of financial operations to be carried out following the commencement of the income generating activity may not mix up with the activities of the charity or society relating to finance.

7. የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴው ወጪና ኪሳራ አግባብ ባላቸው የንግድ ህጉ ድንጋጌዎች መሠረት ከተሰላ በኋላ የሚገኘው የተጣራ ትርፍ በገቢ ማስገኛ ተቋሙ የሂሳብ ሠራተኛ አማካኝነት ወደ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሂሳብ እንዲገባ መደረግ ይኖርበታል፡፡

## 40. አስተዳደራዊ ጉዳዮች

1. የገቢ ማስገኛ ስራ አስተዳደር ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የተለዩና የዕለት ተዕለት ስራዎችን የሚያከናውኑ የራሱ ስራ አስኪያጅና ሂሳብ ሹም ይኖሩታል፡፡

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀፅ 1 ስር የሰፈረው ድንጋጌ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የገቢ ማስገኛ ስራውን በበላይነት ከመቆጣጠር አያግደውም ፡፡

## 41. ስለመፍረስ

1. የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴው በመክሰር፣ በሚመለከተው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ውሳኔ ወይም በቢሮው ትዕዛዝ በሚዘጋበት ወይም በሚፈርስበት ጊዜ ያሉ እንደሆነ የባለገንዘቦች መብት ተከብሮ ሀብትና ንብረቱ ወደ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ወደ ማህበሩ እንዲተላለፍ ይደረጋል፡፡

7. The net profit generated following the calculation of expenses and losses of the income generating activity in accordance with the relevant provisions of the commercial code shall be caused to be deposited in the account of the charity or society on the part of the accountant belonging to the income generating facility.

## 40. Administrative Matters

1. The administration of the income generating activity shall have a manager and an accountant of its own distinct from those of the charity or society and thereby capable of carrying out day- to-day activities.

2. The provision laid down under Sub-Art. 1 hereof, may not bar the charity or society from duly supervising over the income generating activities per se.

## 41. Dissolution

1. Whenever an income generating facility is closed or dissolved due to bankruptcy, decision of the charity or society concerned or order of the Bureau, its assets and properties shall be subject to transfer onto the charity or society after having observed the rights of creditors.

2. የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴው የተዘጋው ወይም የፈረሰው በበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም በማህበሩ ህጋዊ ሰውነት ማብቃት ምክንያት የሆነ እንደሆነ የባለገንዘቦች መብት ተከብሮ ሀብትና ንብረቱ በቢሮው ውሳኔ ተመሳሳይ ዓላማ ላላቸው ድርጅቶች ይተላለፋል፡፡

3. የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴው ሲዘጋ ወይም ሲፈርስ ሊነሱ የሚችሉትን የንብረት ክፍፍል ጉዳዮች አወሳሰን በሚመለከት ቢሮው ይህንን ደንብ ተከትሎ መመሪያ ያወጣል፡፡

## 42. ስለኦዲት ሪፖርት አቀራረብ

1. የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ከመደበኛ ሪፖርታቸው የተለየና የገቢ ማስገኛ ስራውን የገንዘብ እንቅስቃሴ ሊያሳይ የሚችል አመታዊ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅተው ለቢሮው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

2. የኦዲት ሪፖርቱ አቀራረብና ይዘት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

2. Where the closure or dissolution of the income generating activity is attributive to the expiry of legal personality of the charity or society, its assets and properties shall, with the decision of the Bureau, be transferred to those organizations having similar objectives following due regard for the rights of the creditors.

3. The Bureau may issue a directive in pursuance of this regulation as regards the determination of cases that might rise with respect to division of assets in the aftermath of the closure or dissolution of the income generating facility.

## 42. Submission of Audit Report

1. Charities or societies shall prepare and submit to the Bureau an annual audit report distinct from their regular repots and capable of showing the financial activities of the income generating facility.

2. The submission and content of the audit report hereof shall be determined by the directive to be isuued by the Bureau.

## 43. አስተዳደራዊ ቅጣት

1. ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር፡-

ሀ) በዚህ ደንብ መሠረት ከቢሮው የጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኝ በገቢ ማስገኛ ስራ ላይ ተሰማርቶ ከተገኘ፤

ለ) በዚህ ደንብ ከተደነገገው ውጪ ከገቢ ማስገኛ ስራው የሚያገኘውን ትርፍ ለተጠቃሚዎች ወይም ለአባላት ካከፋፈለ፤

ሐ) ለገቢ ማስገኛ ስራዎች የተለየ የሂሳብ መዝገብ ካልያዘ፣ የተለየ የባንክ ሂሳብ ካልከፈተ ወይም የገንዘብ እንቅስቃሴውን ከድርጅቱ ወይም ከማህበሩ ሒሳብ ጋር ከቀላቀለ፤

መ) ለመልካም ስነ-ምግባር ተቃራኒ በሆነ የገቢ ማስገኛ ስራ ላይ ተሰማርቶ ከተገኘ፤

ሠ) ከገቢ ማስገኛ ስራው የሚያገኘውን ገቢ ለዋናው በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር አስተዳደራዊ ወጪዎች መሸፈኛነት ካዋለ፤ እንደነገሩ ሁኔታና እንደጥፋቱ ክብደት ቢሮው ከፅሁፍ ማስጠንቀቂያ

## 43. Administrative Penalty

1. The Bureau may, having due regard to the circumstances and according to the degree of the offence, take such measures ranging from written warning upto the revokaion of the licence against the charity or society where the latter has:

A. been found engaging in an income generating activity without having acquired a written permit pursuant to this Regulation;

B. distributed the profit obtained from its income generating activity to the beneficiaries or members in contravention of the provisions of this regulation;

C. failed to maintain a separate book of account concerning its income generating activities, to open a separate bank account or mixed up its own financial activity with that of the charity or society thereof;

**D.** been found engaging in an income generating activity contrary to good ethical conduct;

E. deployed the income obtained from its income generating activity to cover the administrative expenses of the principal charity or society.

አንስቶ እስከ ፈቃድ ስረዛ የሚደርሱ እርምጃዎችን ሊወስድበት ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) ስር የተመለከቱት አድራጎቶች ጥፋተኛውን አግባብ ባላቸው የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች መሰረት ከመጠየቅ አያድኑትም፡፡

## 44. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. ቀደም ሲል የቢሮውን ፈቃድ ሳያገኙና ስልጣን ካለው የመንግስት አካል የንግድ ፈቃድ ሳያወጡ በገቢ ማስገኛ ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ይህ ደንብ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ እየቀረቡ አስፈላጊውን ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

2. ከዚህ በፊት የንግድ ፈቃድ አውጥተው የንግድ ስራ በማከናወን ላይ ያሉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ይህ ደንብ በዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ጊዜ ዉስጥ በቢሮው ቀርበው ከደንቡ ጋር በተጣጣመ አኳኃን ራሳቸውን ማደራጀት ይኖርባቸዋል፡፡

2. The acts indicated under Sub-Art. 1 of this Article hereof may not exonerate the offender from being prosecuted in accordance with the relevant provisions of criminal code.

## 44. Transitory Provisions

**1.** Those charities and societies which are found to have previously engaged in an income generating activity without having obtained permit from the Bureau and thereby acquired a business license from the authorized government body shall be issued with the necessary license within six months from the date of the effective date of this regulation.

2. Those charities and societies operating commercial activity by having previously obtained a business license shall appear before the Bureau and reorganize themselves and get registered inconformity with the regulation until the expiry of six months starting from the date of publication of this regulation in the Zikre Hig Gazette.

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## ስለህዝባዊ መዋጮ

### 45. ስለፈቃድ አሰጣጥ እና አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች

1. ህዝባዊ መዋጮ ለማካሄድ የሚፈልግ ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማኀበር መዋጮው ሊካሄድ ከታሰበበት ቀን አንድ ወር ቀደም ብሎ ስለዚሁ ለቢሮው በፅሁፍ ማመልከት ይኖርበታል፡፡
2. ህዝባዊ መዋጮ ለማካሄድ የሚያስችል ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም በማህበሩ የበላይ አካል ወይም የስራ ሀላፊ የሚፈረም ሆኖ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡-
   ሀ) ህዝባዊ መዋጮ የሚደረግበት የበጎ አድራጎት ዓላማ/ዎች፣
   ለ) ህዝባዊ መዋጮውን ለማድረግ የተወሰነበት ምክንያት እና ህዝባዊ መዋጮ ማድረጉ ዓላማውን ለማሳካት ያለው ጠቀሜታ፤
   ሐ) ሕዝባዊ መዋጮው የሚካሄድበት ቦታ/ዎች፤
   መ) ህዝባዊ መዋጮው የሚጀመርበትና የሚጠናቀቅበት ቀን፤
   ሠ) ሕዝባዊ መዋጮው የሚካሄድበት ዘዴ/ዎች፤

## SUBPART TWO
## PUBLIC COLLECTIONS

### 45. Issuance of License and necessary Preconditions

1. Any charity of society desiring to conduct public collection shall apply to the Bureau in writing one month prior to the date on which it is intended to carry out such collection.
2. An application for a permit to conduct public collection shall, having been duly signed by the superior organ or officer of the charity or society, contain the following information:
   A. objective/s of the charitable organization to which the public collections would be conducted;
   B. grounds of the decision to conduct the public collections and the benefit of carrying out such an action with a view to achieving its objective;
   C. place/s in which the public collections might be conducted;
   D. date of the commencement and completion of the public collections;
   E. method/s of carrying out the public collections;

ረ) ሕዝባዊ መዋጮውን በበላይነት የሚመራውን/የሚመሩትን የስራ መሪ/የስራ መሪዎች ወይም ግለሰብ/ግለሰቦች የሚመለከቱ መረጃዎች፤

ሰ) ህዝባዊ መዋጮውን ለማካሄድ የሚያስችል የበጀት የአፈፃፀምና የድርጊት መርሃ ግብር፤

ሸ) በህዝባዊ መዋጮው ይገኛል ተብሎ የሚገመተው የገቢ መጠን፤ እና

ቀ) በቢሮው የሚጠየቁ ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች ዝርዝሮች፡፡

3. በህዝባዊ መዋጮ ፈቃድ ላይ እንደነገሩ ሁኔታ መዋጮው ከሚሰበሰብበት ቦታ፣ ባህሪ፣ ዓይነት፣ ዘዴ፣ ቀን፣ የጊዜ ርዝመት እና ከሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ገደቦች በቢሮው አማካኝነት ሊቀመጡ ይችላሉ፡፡

## 46. ፈቃድ ስለመከልከል

1. በአዋጁ አንቀጽ 95 እና 96 ስር የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቢሮው ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜ፡-

ሀ) የህዝባዊ መዋጮ ሊሰበሰብ የታቀደበት ዘዴ፣ ቀን፣ የአሰባሰቡ ድግግሞሽ

F. information regarding those officer/s or individual/s who would be supervising over the public collections;

G. budget implementation and action plan that would enable to conduct the public collections;

H. the amount of income intended to be generated through the public collections; and

I. other particulars to be requested for by the Bureau and connected therewith.

3. Restrictions having to do with the place, nature, kind, method, date, duration and other relevant factors may be imposed by the Bureau with regard to the permit issued for conducting public collection.

## 46. Denial of Permit

1. Without prejudice to the provisions of Arts. 95 and 96 of the Proclamation, the Bureau shall, while issuing permit, have the power to partially or wholly deny, postpone for another time or issue permit, having set pre-conditions to be fulfilled subsequently, where:

A. it is convinced that the method, date, frequency of carrying out the collection or the place intended

ወይም የታሰበበት ቦታ በህብረተሰቡ ላይ አላስፈላጊ ጫናን የሚፈጥር ነው ብሎ ሲያምን፣

ለ) የህዝባዊ መዋጮ አሰባሰቡ እንዲካሄድ የተፈቀደበት ሁኔታ ከሌላ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ተግባር ጋር መደራረብ የሚፈጥር ሆኖ ከተገኘ፣

ሐ) የህዝባዊ መዋጮ ማሰባሰቢያ ዘዴው ውጤታማነት አጠራጣሪ ሆኖ ሲገኝና ለመዋጮው ማከናወኛ የሚወጣው ገንዘብ ከሚገኘው ገቢ ጋር ሲነጻጸር የተጋነነ ሆኖ ከታየ፣

መ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ከዚህ በፊት በተሰጠው የህዝባዊ መዋጮ አሰባሰብ ፈቃድ ውስጥ የተመለከቱትን ግዴታዎች እንዳልተወጣ የሚታወቅ ከሆነ፣

ሠ) ሕዝባዊ መዋጮ ለመሰብሰብ እንዲፈቀድለት ጥያቄ ያቀረበው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ቀደም ሲል ህግን በመጣሱ ምክንያት በቢሮውና በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት በኩል አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶበት ከነበረ፣

ረ. የሕዝባዊ መዋጮ አሰባሰቡን ስራ እንዲያስተባብሩ በበጎ አድራጎት

conducting the public collections would somehow create unnecessary burden on the community;

B. it is found out that the condition in which the undertaking of the public collection has been authorized would likewise create an overlapp with the activity of another charity or society;

C. it is established that the method of carrying out the public collections in view would rather be ineffective and the amount of funds to be invested for undertaking the said collection is over exaggerated to the income which might be generated threfrom;

D. it is recognized that the charity or society has been unable to discharge the obligations indicated in the permit issued previously in its favour;

E. an administrative measure was previously taken against the charity or society requesting for authorization to carry out the public collections by the Bureau and the pertinent government bodies due to its violation of laws;

F. it has been ascertained that individuals who are entrusted with a

ድርጅቱ ወይም በማህበሩ አማካኝነት ሃላፊነት የተሰጣቸው ግለሰቦች ራሳቸው መልካም ስነ-ምግባር የሌላቸውና ከዚህ በፊት በእምነት ማጉደል ወይም በማጭበርበር ድርጊት ተፈርዶባቸው ወይም አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶባቸው ያውቅ እንደሆነ፤ ፈቃዱን በከፊል ወይም በሙሉ የመከልከል፣ ለሌላ ጊዜ የማስተላለፍ ወይም ሊሟሉ የሚገባቸውን ቅድመ-ሁኔታዎች በማስቀመጥ ፈቃዱን የመስጠት ስልጣን ይኖረዋል::

2. ቢሮው ፈቃዱን ከሰጠ በኋላ ፈቃዱን የሰጠባቸው ሁኔታዎች የተለወጡ ወይም ሊለወጡ የሚችሉበት ሁኔታ የተፈጠረ እንደሆነ የሰጠውን ፈቃድ ለተወሰነ ጊዜ ማገድ፣ መሰረዝ ወይም ያስቀመጣቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ይዘት መለወጥ ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ቢሮው የሰጠውን ፈቃድ ሲያግድም ሆነ ሲሰርዝ ወይም ያስቀመጣቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ሲቀይር ይህንኑ ውሳኔውን ከነምክንያቶቹ ለበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ለማህበሩ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 47. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ግዴታዎች

1. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሰረት ህዝባዊ መዋጮ ለመሰብሰብ ፈቃድ የተሰጠው

responsibility to coordinate the public collections activities by the charity or society do not have good ethical conduct or it is known that an administrative measure has been taken against them due to acts of breach of trust or deceit.

2. The Bureau may suspend for an indefinite period of time, revoke the permit it has issued or change the content of the preconditions set forth where the conditions in which it has issued the permit have been altered or the situations of their possible alteration has taken place.

3. Where the Bureau suspends or revokes the permit it has already issued or changes the preconditions which it had set forth in accordance with Sub-Art. 2 of this Article hereof, it shall communicate its decision along with justifications to the charity or society in writing.

## 47. Obligations of the Charity or Society

1. Any charity or society duly authorized to carry out public collections in

ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የተባለውን መዋጮ እንዲሰበስብለት ያሰማራው ወይም የወከለው ሰው በደንቡና በሌሎች ህጎች የተቀመጡ ድንጋጌዎችን አክብሮ ስለመንቀሳቀሱ በቅርብ የመከታተል ግዴታ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ህዝባዊ መዋጮውን እንዲሰበስብለት ያሰማራውን ወይም የወከለውን ሰው ሙሉ ስም እና አድራሻ መዝግቦ የመያዝ እና ከዚህ በታች የተመለከቱትን ዝርዝሮች ስለማሟላቱ የማረጋገጥ ሀላፊነትይኖርበታል፡-

ሀ) እድሜው ከአስራ ስምንት ዓመት ያላነሰ መሆኑን፤

ለ) የዚህን ደንብ ይዘትና በመዋጮ ስብሰባው ወቅት የሚከለከሉ ድርጊቶችን ጠንቅቆ የሚያውቅ መሆኑን፤

ሐ) እንደ ህዝባዊ መዋጮው ዓይነትና መጠን ስራውን ለማከናወን አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ብቃት ያለው መሆኑን፤

pursuance of the Proclamation and this Regulation shall the obligation to closely follow up that the person whom it has deployed or appointed as an agent to carry out the collection on its behalf will have acted with due observance of the provisions laid down in the regulation and other laws.

2. Without prejudice to the general provision stipulated under Sub-Art. 1 of this Article hereof, the charity or society shall maintain having registered the full name and address of the person whom it had charged or delegated with the task of carrying out the public collections and thereby the responsibility to ascertained that he has fulfilled with other details specified below:

A. that he is not less than eighteen years old;

B. that he is fully aware of the content of this regulation and those acts prohibited while carrying out the collection.

C. that he is physically and psychologically fit to carry out the task, depending on the kind and amount of the public collection in view;

መ) በህግ አስቀድሞ ክልከላ ያልተደረገበት መሆኑን፤

3. የህዝባዊ መዋጮ አሰባሰብ ስራውን የሚያካሂደው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መዋጮውን እንዲሰበስቡለት የሚያሰማራቸው ሰዎች፡-

ሀ) የድርጅቱን ወይም የማህበሩን እና የሰብሳቢውን ግለሰብ ስም በግልጽ የሚያሳይ ሆኖ የመዋጮ አስተባባሪ ፊርማ እና የድርጅቱ ወይም የማህበሩ ማህተም ያረፈበት መለያ ወይም የደረት ባጅ፤

ለ) የድርጅቱ ወይም የማህበሩ ማህተም ያረፈበት ሆኖ ከቢሮው የተሰጠውን የህዝባዊ መዋጮ አሰባሰብ መፍቀጃ ደብዳቤ ወይም ሰርተፍኬት ቅጅ፣ በማስረጃነት እንዲይዙ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

4. መዋጮው የሚሰበሰበው በፖስታ፣ በደረሰኝ ወይም በሳጥን ሲሆን የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሁሉም ፖስታዎች፣ ደረሰኞችና ሳጥኖች የየራሳቸው መለያ ቁጥር ያላቸው እንዲሁም የድርጅቱን ወይም የማህበሩን ስም፣ አርማ እና ማህተም የያዙ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

5. ሕዝባዊ መዋጮው ከተሰበሰበ በኋላ መዋጮው የተሰበሰበበት ፖስታ ወይም

D. that he is not barred by law previously.

3. The charity or society carrying out the activity of the public collections shall see to it that those persons whom it had employed to undertake such collections maintain with themselves in the form of an evidence:

A. an identification or a chest badge clearly demonstrating the name of the charity or society and the person in charge of the collecting and bearing the signature of the coordinator of the collections and the seal of the charity or society;

B. the copy of the letter or certificate thereof authorizing the public collections and thereby bearing the seal of the charity or society as rendered by the Bureau.

4. Where the collection is carried out using posts, receipts or boxes, the charity or society shall ensure that all such posts, receipts or boxes have their respective numbers of identification as well as they bear its name, emblem and seal with them.

5. After the completion of the collections, the post or box by which the collections

ሳጥን ሊከፈት የሚችለው ድርጅቱን፣ ማህበሩን ወይም የሕዝባዊ መዋጮውን አሰባሰብ ተግባር በበላይነት በሚመራው ሰው ወይም በእርሱ ተወካይ ፊት ብቻ ይሆናል፡፡

6. በመኖሪያ ቤት አካባቢና እና በሌሎች በተከለሉ ስፍራዎች የሚከናወን ማናቸውም ዓይነት ህዝባዊ መዋጮ የማሰባሰብ ስራ ከቢሮው የተለየና ተቃራኒ ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር ከጧቱ 1፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12፡00 ሰዓት ብቻ መደረግ ይኖርበታል፡፡

## 48. ስለህዝባዊ መዋጮ ሪፖርት አቀራረብ

1. ህዝባዊ መዋጮውን የሚያስተባብረው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የመዋጮው አሰባሰብ በተጠናቀቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ማናቸውም የገንዘብ እንቅስቃሴ እና የሃብት ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርት ለቢሮው ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተጠቀሰው ሪፖርት ከገቢ እና ከወጪ ዝርዝሮች በተጨማሪ የመዋጮ አሰባሰብ ሂደት ማሳየት ይኖርበታል፡፡
3. ቢሮው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መዋጮውን በሚመለከት ማንኛውም መረጃ እንዲቀርብለት የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን ሊጠይቅ ይችላል፡፡
4. ህዝባዊ መዋጮውን ያስተባበረው አካል

have been made may be opened only in front of the officer managing the charity or society or supervising over its task of the public collection thereof.

6. The activity of public collections of whatever type to be carried around residential houses and demarcated places shall be conducted only from 7:00 A.M. through 6:00 P.M. unless a specific permit to the contrary has been granted by the Bureau.

## 48. Reporting on Public Collection

1. The charity or society coordinating the public collection shall submit to the Bureau a report showing any financial activity and state of assets having to do with such collection within three months from the time in which the task was completed.
2. The report cited under Sub. Art. 1 of this Article hereof shall, in addition to of income and expenditure particularities, depcting the process in which the collection has been carried out.
3. The Bureau may, where it finds it necessary, seek for any information regarding the collection to be submitted to it from the charity or society.
4. The body which was entrusted with

ቢሮው ከቀረበለት ሪፖርት ጋር በተያያዘ የሚያነሳቸውን ማናቸውንም ዓይነት ጥያቄዎች መመለስና ተገቢ መረጃዎችን ማቅረብ አለበት፡፡

## 49. ህዝባዊ መዋጮን በኮሚሽን ማከናወን ስለመከልከሉ

ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በመዋጮ ከሚሰበሰበው ሃብት ውስጥ የተወሰነውን ፐርሰንት በመክፈል ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ኮሚሽን ለመክፈል በመስማማት ህዝባዊ መዋጮን ሊያካሂድ አይችልም፡፡

## 50. ሌሎች ግዴታዎች የተጠበቁ ስለመሆናቸው

ቢሮው በዚህ ደንብ ያገኘውን ፈቃድ የመስጠት ስልጣን ህዝባዊ መዋጮ ለማካሔድ እንደአስፈላጊነታቸው በሌሎች ህጎች የተመለከቱትን ግዴታዎች አያስቀርም፡፡

## 51. አስተዳደራዊ እርምጃዎች

1. አግባብ ያላቸው የሀገሪቱ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ ደንብ በተደነገገው መሰረት፡-
   ሀ. ቢሮው ፈቃድ ሳይሰጠው ህዝባዊ መዋጮን በማሰባሰብ ተግባር ላይ ተሰማርቶ የተገኘ እንደሆነ፤

the coordination of the public collections shall respond to any kind of inquiries from and thereby provide appropriate information to the Bureau in connection with the report submitted to it.

## 49. Prohibition of Carrying out Public Collection on Commission

Any charity or society may not be able to carry out public collections by paying a determinate percent of the assets to be collected or in an agreement to pay commission in any other way.

## 50. Sustainance of Other Obligations

The licensing authority vested in the Bureau pursuant to this regulation may not revoke obligations with regard to the carrying out of public collections laid down in other laws, as deemed necessary.

## 51. Administrative Measures

1. Without prejudice to the relevance provisions of the Country’s Criminal Code, where any charity or society pursuant to this Regulation:
   A. is found to have engaged in an activity mobilizing public collections being duly authorized by the Bureau;

ለ. የሚጠበቅበትን ሪፖርት ለቢሮው ሳያቀርብ ወይም ስለመዋጮ አሰባሰቡ ስርዓት የተደነገገውን ሳያከብር የቀረ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታና እንደጥፋቱ ክብደት ከፅሁፍ ማስጠንቀቂያ አንስቶ ላልተወሰነ ጊዜ ከህዝባዊ መዋጮው እንቅስቃሴ እስከመታገድ የሚደርስ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድበት ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ አንቀፅ 1 ስር የተጠቀሰው አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ የስራ መሪን ከሃላፊነት ስለማንሳት፣ የበጐ አድራጐት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን ስለማገድ፣ ስለማፍረስ እና እነዚህን ስለመሳሰሉ ሌሎች እርምጃዎች የአዋጁ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ስድስት
## ንብረቶችን ስለማጣራት፣ ስለማስተላለፍና ስለማስወገድ

### 52. ንብረት አጣሪዎችን የመሾም ወይም የመሠየም ስልጣን

1. በህግ አግባብ የፈረሱ ወይም የተሰረዙ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ሲኖሩ ሀብትና ንብረታቸው የሚጣራው ቢሮው በሚሰየማቸው ወይም

B. failed to submit the report required of it to the Bureau or observe the stipulations laid down with regard to task of public collections, it may, having due regard to the circumstances and according to the degree of the offence, be subject to administrative measures ranging from written warning through suspension from engaging in such collections for indefinite period of time.

2. Without prejudice to the administrative measure referred to under Sub-Art. 1 this Article hereof, the relevant provisions of the Proclamation shall apply in respect of the removal from office of the director as well as the suspension from duty, dissolution of the charity or society and other measures.

## PART SIX
## LIQUIDATION , TRANSFER AND DISPOSSAL OF PROPERTY

### 52. Power to Appoint or Designate Liquidators

1. Where there exist charities or societies dissolved or revoked in accordance with laws, their assets and properties shall be examined by the liquidators to be either

ፍርድ ቤት በሚሾማቸው ንብረት አጣሪዎች ይሆናል፡፡

2. አጣሪዎች የሚሾሙት በሙሉ ፈቃደኝነትና ፍላጐት ይሆናል፡፡

## 53. የንብረት አጣሪዎች ስብጥር

1. አጣሪዎች ስራቸውን የሚያከናውኑት በኮሚቴ ተዋቅረው ሲሆን የዚሁ ኮሚቴ አባላት ጥንቅር ከሚከተሉት የተውጣጣ ይሆናል፡-
   ሀ. ቢሮው የሚሰይማቸው ሰራተኞች፣
   ለ. ንብረቱ የሚጣራለት የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የስራ መሪዎችና ባልደረቦች፣
   ሐ. ለማጣራት ስራው የሚያስፈልጉና አግባብነት ያላቸው የዘርፍ አስተዳዳሪዎች እና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት፡፡

2. የአጣሪ ኮሚቴው አባላት ቁጥር እንደየሚጣራው ንብረት ስፋትና ብዛት እየታየ በሿሚው አካል የሚወሰን ሆኖ በጠቅላላው ከአምስት (5) የሚዘል አይሆንም፡፡

designated by the Bureau or appointed by court.

2. Liqudators shall be appointed on the basis of their full consent and desire.

## 53. Composition of Property Examiners

1. The liquidators shall carry out their duty having been structured in a committee, membership of which shall be drown from the following:
   A. employees to be designated by the Bureau;
   B. the officers and staff of the charity or society whose property is to be examined;
   C. the relevant sector administrators and non-governmental bodies which might be necessary for the duties of the examination thereof.

2. The number of members of the examining committee is subject to determination by the appointing body in consideration of the volume and quantity of the property waiting to be examined; provided, however, that its total size may not exceed five (5).

## 54. የንብረት አጣሪዎች ስልጣንና ተግባር

ንብረት አጣሪዎች በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ስልጣና ተግባራት ይኖሯቸዋል፡-

1. ንብረት የማጣራትና የማስተላለፍ ሥራዎችን ነፃና ገለልተኛ በመሆን ያከናዉናሉ፤
2. የኦዲት ሪፖርቶችን፣ የሒሳብ መግለጫዎችንና የንብረት ዝርዝሮችን ጨምሮ የማጣራት ሥራቸውን ለማከናወን አስፈላጊ ሆነው የሚያገኟቸውንና አግባብነት ያላቸውን ማናቸውንም ሰነዶችና ማህደሮች አስቀርበው ይመረምራሉ፣ ተዛማጅ መረጃዎችን ይሰበስባሉ ያጠናቅራሉ እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የበጎ አድራጎቱ ወይም የማህበሩ ሥራ መሪዎች ቀርበው እንዲያስረዱ ያደርጋሉ፤
3. በሒደቱ ውስጥ በንብረት ማጣራትና ማስተላለፍ ሂደቱ ተገቢ ሆኖ ሲያገኙት መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ሙያዊ እገዛ ይጠይቃሉ፤
4. የማጣራት ስራው በሚከናወንበት ወቅት በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም በማህበሩ ይዞታ ስር የሚገኝ ማናቸውንም የንብረት ማከማቻ ክፍል ያሽጋሉ፣

## 54. Powers and Duties of Property Liquidators

Liquidators shall, pursuant to this regulation, have the following powers and duties:

1. carrying out their dutes of liquidation and transfer with independence and neutrality;
2. cause the presentation of and thereby investigate those relevant documents and files including the audit reports, financial statements and property detail which they would find necessary to carry out their examination, collect and compile information related thereto as well as secure the appearance and testimony of the officers belonging to the charity or society concerned with the issue;
3. seek for professional support from governmental and non-governmental bodies should they find throught out the process;
4. temporarily close any property store within the possessions of the charity or society during the lidudation process;

5. የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን ኃብቶችና ዕዳዎች የስርጭት ምጣኔ በመለየት ዝርዝር የሃብትና ዕዳ ሚዛን ያዘጋጃሉ፤
6. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ የሃብትና ዕዳ መጠን የግድ በውጭ ኦዲተር መመርመር ያለበት ሆኖ ሲገኝ ይኸው በራሱ ወጭ እንዲከናወን ያሳስባሉ፤
7. ይበላሻል ወይም ለከፍተኛ ወጪ ይዳረጋል ተብሎ የተገመተ ንብረት ቢኖር ይኸው በወቅቱ በገበያ ዋጋ ተሽጦ ገንዘቡ በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም በማህበሩ ስም ዝግ ሒሳብ ተከፍቶለት በባንክ እንዲቀመጥ ያደርጋሉ፤
8. በመጣራት ሒደት ላይ ያሉ ንብረቶች ሳይመዘበሩ፣ ሳይባክኑና ሳይበላሹ ተጠብቀው እንዲቀመጡ ያደርጋሉ ፣
9. የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን ልዩ ልዩ ወጪዎችና ዕዳዎች በስሙ ይከፍላሉ ወይም እንዲከፈል ያደርጋሉ፣ ስለዚሁ ደረሰኝ ይቀበላሉ፣ ይሰጣሉ፤
10. የማጣራት ሥራው ከተጠናቀቀና የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ወጪዎችና ዕዳዎችም ተከፍለው ካለቁ በኋላ የቀረ ሀብት ቢኖር በአዋጁ፣ በዚህ ደንብና ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለሚገባው አካል ያስተላልፋሉ፤

5. to prepare the balanced sheet of assets and liabilities belonging to the charity or society by having identified the proportional distribution of its credits and debts thereof ;
6. where the extent of assets and liabilities referring to the charity or property has as of necessity, to be inquired into by an external auditor, recommend that such an auditing to be carried out against on its own expense;
7. where there exists an asset which is considered to be spoiled or likely to perish with a disproportionate expense, cause same to be sold in a current market price and the mony deposited in a blocked bank account in the name of a charity or society;
8. cause the protection and maintainance of properties pending liquidation free from embezzlement, wastage or spoilage thereof;
9. pay out or cause the payment of various expenditures and debts in the name of charity or society as well as accept and issue receipts to that effect;
10. transfer the remaining assets, if any, to the appropriate organ entitled thereto pursuant to the proclamation, this regulation and directive to be issued by the Bureau after the liquidation has been completed as well as payment of the expenses and debts pertaining to

11. የስራ እንቅስቃሴያቸውን በተመለከተ ወቅታዊ ዘገባዎችን እያዘጋጁ ለሾማቸው አካል ያቀርባሉ፡፡

## 55. አጣሪዎችን ስለማንሳትና በሌሎች ስለመተካት

የትኛውም ንብረት አጣሪ በማናቸውም ምክንያት የአጣሪነት ተግባሩን ማከናወን አለመቻሉን ሿሚው አካል የተረዳ እንደሆነ ከኃላፊነቱ ሊያነሳውና በሌላ ሊተካው ይችላል፡፡

## 56. የንብረት አጣሪዎች የህግ ተጠያቂነት

1. ማናቸውም ንብረት አጣሪ ከማጣራት ሥራው ጋር በተያያዘ ይህንን ደንብ በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ አግባብ ባላቸው የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም ንብረት አጣሪ በሚያጣራው ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ለሚያደርሰው ጉዳት በፍትሐብሔር ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 57. የንብረት ማጣራት ሥርዓት

ቢሮው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን ንብረት ለማጣራት የሚያስፈልገውን ዝርዝር የአሰራር መመሪያ ያወጣል፡፡

the charity or society has been settled;

11. prepare periodic reports pertaining to their activities and thereby submit same to the body responsible for their appointment.

## 55. Removal of Liquidators and Their Substitution by Others

Where the appointing body is aware that any liquidator has been unable to discharge his duties for any reason, it may remove and duly substitute him by another;

## 56. Legal Liabilities of Liquidators

1. Any liquidator found to have committed offense in relation to his duties contrary to this regulation; he shall be liable in accordance with the relevant provisions of the criminal code.
2. Any liquidator who may intentionally or by negligence caused harm to property under his investigation shall be liable in accordance with the civill code.

## 57. Procedure of Liquidation

The Bureau shall issue a specific directive of working procedure necessary to carry out the liquidation in respect of charities or societies.

## 58. ንብረት ወይም ሀብት ስለማስተላለፍ

1. የበጎ አድራጎት ድርጂቱ ወይም ማህበሩ ወጭዎችና እዳዎች ተከፍለው ከተጠናቀቁ በኋላ የተገኘ ቀሪ ሀብት ቢኖር ወደ ሌሎች የሚተላለፈው ከዚህ በታች በተመለከተው ቅደም-ተከተል ይሆናል፡-
   - ሀ. ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ዓላማ ያለው የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር፤
   - ለ. ልዩ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል ብሎ ቢሮው ያመነባቸው የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ወይም ማህበራት፤
   - ሐ. ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ከማህበሩ ጋር ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ዓላማ ያላቸው ሆነው ማህበራዊ አገልግሎት ለሚሰጡ መንግስታዊ ተቋማት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር በተደነገገው መሰረት የሚተላለፈው ንብረት መጠን ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ አጣሪዎች ይህንኑ ሁለትና ከዚያ በላይ ለሆኑ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ሊያስተላልፉ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## 58. Transfer of Property or Assets

1. The assets and properties remained following the completion of payment as regards the expenditures and debts of the charity or society thereof, the remaining property, if available, shall be transferred onto others in compliance with the priorities indicated here below:
   - A. a charity or society having similar or related objectives;
   - B. charities or societies which the Bureau believes are in need of special support;
   - C. governmental institutions in charge of providing social services and having objectives similar or related to those of the charity or society.
2. Where the amount of property subject to transfer pursuant to what has been stipulated under Sub-Art. 1 of this Article hereof is enormous; liquidators may be able to pass same onto two and more charities and societies. Particulars shall be determined by a directive which the Bureau may issue.

## 59. ስለንብረት ማስወገድ

ቢሮው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና የማህበራትን የንብረት አወጋገድ በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

## 59. Disposal of Property

The Bureau shall issue a specific directive as regards the disposal of property belonging to charities and societies.

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## PART SEVEN

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 60. የጥቅም ግጭት

1. አንድን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በመወከል ከሶስተኛ ወገን ጋር ግንኙነቶችን በሚያደርግበት ጊዜ በድርጅቱ ወይም በማህበሩ እና በእርሱ መካከል የጥቅም ግጭት መከሰቱን ያወቀ ማንኛውም የሥራ መሪ ወይም ተወካዩ ይህንኑ ክስተት ለሚመለከተው የድርጅቱ ወይም የማህበሩ የበላይ አካል ወዲያውኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ቢሮው ወይም ማንኛውም ሰው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር እና የሥራ መሪ ወይም ተወካዩ መካከል የጥቅም ግጭት መከሰቱን ያወቀ እንደሆነ ይህንኑ ለድርጅቱ ወይም ለማህበሩ የማሳወቅ መብት ይኖረዋል፡፡
3. የጥቅም ግጭቱ ስለመከሰቱ መረጃ የደረሰው እና አግባብ ያለው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ይኸው ግጭት በተከሰተበት ግንኙነት መቀጠል ወይም መቋረጥ ጉዳይ ላይ አጠቃላይ ጥቅሞችን መሰረት አድርጎ

## 60. Conflict of Interest

1. Any officer or his agent who is aware of the creation of conflict of interests between a charity or society and himself while dealing with third parties on behalf of the former shall be obliged to immediately inform such an incident to the superior body of the charity or society concerned.
2. Without prejudice to the provision of Sub-Art. 1 of this Article hereof, the Bureau or who so ever is aware of the existence of conflict of interests between a charity or society and its officer or his agent shall have the right to communicate such an incident to the charity or society.
3. The pertinent body of the charity or society having been provided with the information as to the existence of the conflict of interests shall, decide on the sustenance or termination of the relationship affected by such conflict,

ይወሰናል፡፡ ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ከማህበሩ ጋር ጥቅም ግጭት ውስጥ የገባው የሥራ መሪ ወይም ተወካዩ በዚህ ውሳኔ አሰጣጥ ሊሳተፍ አይችልም፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የተሰጡ ውሳኔዎች ተመዝግበው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት አካል ሆነው ለቢሮው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

5. በአዋጁ አንቀጽ 86 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር በተደነገገው መሠረት የጥቅም ግጭት መፈጠሩን ያላሳወቀ የሥራ መሪ ወይም ተወካዩ በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

## 61. የምዝገባ የምስክር ወረቀትን በይፋ ስለማሳየትና ስለማስታወቂያ ሰሌዳ አጠቃቀም

1. በአዋጁ አንቀጽ 70 ስር የተደነገገውን ያላከበረ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ተፈላጊውን እንዲፈጽም ቢሮው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡

having taken broader interests into account; provided, however, that the officer of the charity or society or his agent involved in the said conflict may not participate in the decision making process.

4. The decisions made pursuant to Sub-Art. 3 of this Article hereof shall be recorded and thereby submitted to the Bureau, being part of the annual activity reports of the charity or society.

5. Without prejudice to the provision of Art. 86 of the Proclamation, an officer or his agent failing to inform the existence of a conflict of interest in accordance with Sub-Art. 1 of this Article hereof shall be subject to the action prescribed by the rules of the charity or society.

## 61. Displaying Registration Certificate and Use of Notice board

1. The Bureau may serve a written warning on any charity or society which may have failed to observe the provisions of Art. 70 of the Proclamation so that it would implement what is required of him within a defined period of time.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጥ ማስጠንቀቂያ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊሰጥ አይችልም፡፡

## 62. ስለቢሮው ትዕዛዞች

1. ቢሮው በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ለማህበራት የሚሰጠው ማናቸውም ትዕዛዝ በጽሁፍ ሆኖ ግዴታው በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መፈፀም እንዳለበት የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል፡፡
2. ትዕዛዙ የተሰጠው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበርም የትዕዛዙን አፈጻጸምና የተፈፀመበትን ቀን ለቢሮው በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
3. የማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሥራ መሪ የአዋጁን፣ የዚህን ደንብ ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌዎች በሚጥስበት ጊዜ ጥፋቱን እስኪያርም፣ በወንጀል ተከሶ ፍርድ እስኪያገኝ ወይም በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት በሌላ እስኪተካ ድረስ በቢሮው አማካኝነት ለጊዜው ከኃላፊነት ሊታገድ ይችላል፡፡

2. The warring issued pursuant to Sub-Art. 1 of this Article hereof may not be rendered more than once.

## 62. Orders of the Bureau

1. Any order which the Bureau may issue for charities or societies in accordance with the Proclamation or this Regulation shall be in writing and capable of stating the time limit in which the obligation contained therein has to be performed.
2. The charity or society addressed with the order shall notify in writing in the execution of such an order along with the date to the Bureau.
3. Where an officer of any charity or society violates the provisions of the Proclamation, this Regulation or rules of the charity or society, he may temporarily be suspended from office by the Bureau until such time that he will have rectified his misdeed, prosecuted and received sentence in criminal action or been replaced by another pursuant to the rule of the charity or society.

4. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ለጊዜው የታገደ ለዕገዳው መነሻ የሆኑትን ጥፋቶች በምን ያህል ጊዜ ማስተካከል እንደሚገባው የሚገልጽ የጽሁፍ ትዕዛዝ መስጠት ይኖርበታል፡፡

## 63. ስለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ቅሬታ ሰሚ ጉባኤ

1. በአዋጁ አንቀጽ 98 ስር የተመለከተው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ቅሬታ ሰሚ ጉባዔ አባላት የአገልገሎት ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም ለተጨማሪ የአገልገሎት ዘመን ከመሰየም አይታገዱም፡፡
2. ማንኛውም የቅሬታ ሰሚ ጉባዔ አባል የሞተ፣ ስራውን የለቀቀ ወይም ከኃላፊነቱ የተነሳ እንደሆነ በቀሪው የአገልገሎት ዘመን ውስጥ እርሱን ተክቶ የሚሠራ አዲስ አባል መሰየም ይኖርበታል፡፡
3. የቅሬታ ሰሚ ጉባዔ አባላት በጉባዔው ስብሰባዎች ላይ እየተገኙ ለሚያበረክቱት አገልግሎት የክልሉ መስተዳደር ም/ቤት ወደፊት በሚያወጣው መመሪያ መጠኑ የሚወሰን የማበረታቻ አበል ሊከፈላቸው ይችላል፡፡

4. The Bureau shall hand a written order over to the officer temporarily suspended pursuant to Sub-Art. 3 of this Article hereof stating the time limit within which he ought to rectify the wrongs which were meant facilitate the suspension thereof.

## 63. Grievance Hearing Commission of Charities and Societies

1. The term of office of members serving in grievance hearing commission of charities and societies indicated under Art. 98 of the Proclamation shall be five years; provided, however, that they may not be barred from being re-designated for additional terms.
2. Where any member of the grievance hearing commission has died, resigned his duty or been removed from office, a new member shall, in his replacement, be designated to serve within the remainder the term.
3. Members of the grievance hearing commission may be paid an incentive allowance whose amount is to be determined by a directive which the council of the Regional Government shall issue for the service they will have provided being present at the meetings of the commission.

4. የቅሬታ ሰሚ ጉባኤ ፀሐፊው የሚከተሉት ዝርዝር ተግባራት ይኖረዋል፡-

ሀ/ የጉባኤውን የውስጥ ጉዳዮች ይመራል፤ ያስተባብራል፣

ለ/ ለጉባኤው የሚቀርቡትን አቤቱታዎች ይቀበላል፤ ይመዘግባል፣

ሐ/ ጉባኤው የሚያሳልፋቸውን ውሳኔዎችና የሚሰጣቸውን ትዕዛዞች አግባብ ላላቸው አካላትና ተጠቃሚ ግለሰቦች ያሰራጫል፤

መ/ የጉባኤውን ሰነዶች ይይዛል፤ ይጠብቃል፣

ሠ/ በጉባኤው ሰብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 64. ሞዴል መተዳደሪያ ደንቦችና ቅጾች

ቢሮው በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች አስፈላጊ የሆኑትን ሞዴል መተዳደሪያ ደንቦችንና ቅጾችን ያዘጋጃል፣ ጥያቄ ሲቀርብለትም ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ይሰጣል፡፡

4. The secretary of the grievance hearing commission shall have the following specific duties:

A. Manage and coordinate the internal affairs of the commission ;

B. Receive and register the petition submitted to the commission;

C. Transmit those decisions passed and orders rendered by the commission to the relevant bodies and private persons likely to benefit therefrom.

D. Keep the custody of and preserve documents belonging to the commission ;

E. Carry out such other related duties as are to be assigned to him by the chairperson of the commission.

## 64. Model Rules and Forms

The Bureau shall, in accordance with the Proclamation and this regulation, prepare model rules and forms necessary for the provision of its services and thereby supply same to charities and societies upon request.

## 65. የአገልግሎት ክፍያዎች

ቢሮው ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚጠይቃቸው የአገልግሎት ክፍያዎች ዓይነትና መጠን ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተው ይሆናል፡፡

## 66. የህግ ተጠያቂነት

ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት፣ ማህበር ወይም ኮሚቴ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የጣሰ እንደሆነ በአዋጁ አንቀፅ 102 እና በሌሎች የወንጀል ህጎች መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 67. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 68. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ቢሮው ለዚህ ደንብ ሙሉ ተፈጻሚነት የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 69. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር

ሐምሌ 19 ቀን 2005 ዓ.ም

አያሌው ጐበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር

## 65. Service Charges

The type and amount of service charges which the Bureau may demand in return for the provision of its services indicated in the Schedule annexed to this regulation.

## 66. Legal Liability

Any charity, society or committee which may have violated the provisions of this Regulation shall be liable in accordance with Art. 102 of the Proclamation and other provisions of the criminal code.

## 67. Inapplicable Laws

Any other regulation, directive or customary practice which contradicts this regulation may not apply to matters provided for therein.

## 68. Power to Issue Directives

The Bureau may issue specific directives necessary for the full implementation of this regulation.

## 69. Effective Date

This Regulation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre Hig Gazette of the Regional State.

Done at BahirDar

This 26th day of July, 2013

Ayalew Gobezie

Head of Government of the Amhara National Regional State

## ሰንጠረዥ

## የአገልግሎት ክፍያዎች

<table>
<tr><th rowspan="2">ተ.ቁ</th><th rowspan="2" colspan="2">የአገልግሎት ዓይነት</th><th colspan="2">የክፍያ መጠን</th></tr>
<tr><th>ብር</th><th>ሣ</th></tr>
<tr><td>1</td><td colspan="2">መደበኛ ምዝገባ</td><td>500</td><td>00</td></tr>
<tr><td>2</td><td colspan="2">ወዲያውኑ ምዝገባ</td><td>400</td><td>00</td></tr>
<tr><td>3</td><td colspan="2">የአርማና ምልክት ምዝገባ</td><td>100</td><td>00</td></tr>
<tr><td>4</td><td colspan="2">የስያሜና የመተዳደሪያ ደንብ ለውጥና መሻሻል ምዝገባ</td><td>100</td><td>00</td></tr>
<tr><td>5</td><td colspan="2">ዕድሳት</td><td>400</td><td>00</td></tr>
<tr><td>6</td><td colspan="2">የተፈረሙና የተረጋገጡ ሞዴል መተዳደሪያ ደንቦች/ለወዲያውኑ ተመዝጋቢዎች/</td><td>100</td><td>00</td></tr>
<tr><td>7</td><td colspan="2">ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎችና ሕዝባዊ መዋጮ ማስፈቀድ</td><td>150</td><td>00</td></tr>
<tr><td>8</td><td colspan="2">የማመልከቻ ቅጽ</td><td>5</td><td>00</td></tr>
<tr><td>9</td><td colspan="2">የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎች ማፀደቂያ</td><td>200</td><td>00</td></tr>
<tr><td>10</td><td colspan="2">የሰነድ ትክክለኛ ቅጅ በገጽ</td><td>5</td><td>00</td></tr>
<tr><td>11</td><td colspan="2">የመተዳደሪያ ደንብ ማስገምገምያ</td><td>200</td><td>00</td></tr>
<tr><td rowspan="2">12</td><td rowspan="2">ጋዜጣ ማሳተሚያ</td><td>ሀ/ በምዝገባ ወቅት</td><td>የወቅቱ የማሳተሚያ ዋጋ</td><td></td></tr>
<tr><td>ለ/ በስያሜ ለውጥ ወቅት</td><td>የወቅቱ የማሳተሚያ ዋጋ</td><td></td></tr>
</table>

# Schedule

## Service Charges

| Roll. No | Service Type | | fee amount | |
|---|---|---|---|---|
| | | | Birr | Cent |
| 1 | Regular Registration | | 500 | 00 |
| 2 | Immediate Registration | | 400 | 00 |
| 3 | Registration for Emblem and Symbol | | 100 | 00 |
| 4 | Registration for the Alteration and Improvement of designation and Rules | | 100 | 00 |
| 5 | Renewal | | 400 | 00 |
| 6 | Signed and verified model Rules for Applicants /for immediate registration/ | | 100 | 00 |
| 7 | For Permission of Income Generating Activities and the Public Collections | | 150 | 00 |
| 8 | For an application form | | 5 | 00 |
| 9 | Fro the Approval of charitable committees | | 200 | 00 |
| 10 | For a copy of an original document per page | | 5 | 00 |
| 11 | For an evaluation of rules | | 200 | 00 |
| 12 | For publicizing in a newspaper | A. At the time of registration | current publishing price | |
| | | B. At the time of alteration of designation | current publishing price | |